# ጥላ TILA

ጥላ ነሃሴ 2004 ዓ.ም አንደኛ ዓመት ቁ 3 TILA August 2012 First Year 3rd Edition

# Where is The Ethiopian Prime Minister? WANTED!






## ወርቃችን

## The Sugar Candy Mountain




**Ethiopian Opposition Party members, on the way of informing the people of Germany about the current situation of Ethiopian politics.**





**``Frankfurt Demonstration against the wrong doings of The Dictatorial Meles regime``19-7-2012**



# ጥላ

ዋና ስራ አስኪያጅ
መስፍን አብርሃ

**General Manager**
**Mesfin Abraha**

## ዋና አዘጋጆች / Editor In Chiefs

እየሩሳሌም ሱሞሮ — **Eyerusalem Sumoro**
ብሩክ ገ/መስቀል (ካርቱኒስት) — **Biruk G/Meskel (Cartoonist)**
ዳዊት ፋንታ — **Dawit Fanta**

## አዘጋጆች / Editors

ዮሃንስ ሳምሶን — **Yohannes Samson**
ብሩክ ሃይሉ — **Biruk Hailu**

## ፅሁፍ አስተባባሪዎች / Coordinators

ዮሴፍ ክፍሌ — **Yosef Kifle**
ኤደን ዳዊት — **Eden Dawit**
ዳንኤል ፋንታ — **Daneil Fanta**
ህይወት ጥላሁን — **Hiwot Tilahun**
ወልደኪሮስ አስፋው — **Weldekiros Asfaw**

## የኮምፒዩተር ፅሁፍ ቅንብር / Computer Graphics

ሩት ተሰማ — **Rut Tessema**
ህሊና ዳዊት — **Hilina Dawit**
ዩናስ ተስፋይ — **Yonas Tesfay**

## ሌይአውትና ዲዛይን / Layout & design

እየሩሳሌም ሱሞሮ — **Eyerusalem Sumoro**


**የጥላ መፅሄት አድራሻ /Tila Magazine Address**

**Mesfin Abraha**
**Löhrgasse Str. 4**
**36251 Bad Hersfeld**
**E-Mail:- tilamagazine@yahoo.de**
**Web- Site:- tilamagazine.yolasite.com**
**Tel.No.:- 0152 22195567, 0176 59384456 ,0176 68830082**

# ማውጫ


ገጽ


**Current Affairs The Sugar Candy Mountain** 7
ትናንትና ዛሬ 9
በቃ!!! 9
ያልተሳካው የተቋማት ግንባታ 9
የሃይማኖት ነጻነት ይከበር!!! 9
የካንጋሮው ፍርድ ቤት ውሎ 9
የግፍ ዘመን ይብቃ 10
የዕድገት ማነቆ 10
መፍትሔ ያጣው የዜጎቻችን ስቃይ 11
በጋራ እንነሳ 11
ግዛኝ ግዛኝ ብለው ለመሸጥ አሰበኝ 11
ሰፊው ህዝብ ያሸንፋል! 11
የኢትዮጵያ ህዝብና የአምባገነኑ ቡድን ፍጥጫ 11
እሳት ከሌለ ጭስ አይኖርም 12
በጋራ እንታገል 13
የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በቅርቡ ወደ መቃብር ይወርዳል 13
የወያኔ የኢንተርኔት ላይ ዘመቻ 13
የጨለማው ቀን 14
ወያኔና የኢትዮጵያን ታሪክ የማጥፋት እቅዱ 14
ሁሉም ይንቃ 14
እሱን ብሎ መሪ 15
ጸረ ትውልድ 15
የወያኔ ተንኮልና መዘዝ 15
የሽብርተኝነት ሥያሜ በኢትዮጵያ 16
የምንታገለው ሥርዐቱን ነው!!! 16
የምንመራው በህግ ወይስ? 16
ስእል 17
የህዝቤ ነፃነት ናፈቀኝ 18
አደራው ለማን ነው 18
መወገድ ያለበት ወያኔ 18
የኢትዮጵያ ህዝብ በወያኔ መንግስት ተጨቁኗል 18
አሽባሪው ማነው? 18

# ማውጫ

ገጽ


| | |
|---|---|
| ፍፃሜው የሚያስደነግጥ የአምባገነኖች ሩጫ | 19 |
| አፈና በዛ | 19 |
| እጅ ለእጅ ተያይዘን ወያኔን ከጭንቅላታችን እናውርድ! | 19 |
| ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ | 20 |
| አምባገነንነት ይብቃ | 21 |
| በአምባገነኑ የወያኔ መንግስት ህዝቡ ሰላምና ነጻነት አጥቷል! | 21 |
| ትግላችንን በያለንበት ቦታ ሆነን እንቀጥል | 21 |
| የነጻነት ጉዞ | 22 |
| ማንም ከተጠያቂነት አይድንም | 23 |
| ጎጂ ልምዶችን ያባባሰ ስርዓት-ወያኔ/ኢህአዴግ | 23 |
| ነጻነት ያለው እኩልነት ይኑር | 23 |
| Adios Freedom of Expression! | 24 |
| Now at the end of dictator MELES ZENAWI!!! | 24 |
| The time to be United! | 25 |
| Why Ethiopian cannot Revolt now? | 25 |
| No Democracy in Ethiopia | 25 |
| Ethiopia is calling –The Time is now | 26 |
| The budget deficit of Ethiopia | 26 |
| Ethiopians Must Awaken, “BEKA!” | 26 |
| The New Anti Terrorism Law- A Weapon against Basic Democratic Rights in Ethiopia | 27 |
| The Events of Woyane State in Ethiopia | 28 |
| Stop State Terrorism in Ethiopia!!! | 28 |
| What comes next in Ethiopia? | 28 |
| Unity and Independence | 29 |
| Diktatorische Regierung des Meles Regimes | 29 |
| The Key Elements of Good Governance | 30 |
| Woyane is still cheating the world! | 31 |
| ደረሰ ሰዓቱ ! | 32 |
| እስከ መቼ ልመና | 32 |
| መሪ ያጣች አገር | 32 |



# Editorial

## Yours End Goal will be Great!

As it is already known, in the previous editions of Tila Magazine we were vehemently urging those dispersed opposition groups to come together and struggle under the governance of one goal and purpose.

So seeming to in favour of our very idea, the last 3 Months the Ethiopian People's Congress United Struggle(Shengo)&Ethiopian National Transitional Council have been established.




And the primary goal of these institutions is to arrange a conducive situation for the creation of all-inclusive Ethiopian Transitional Government that will replace the current regime.


In fact, following to the call of Gen. Kemal Gelchu's OLF on Dec. 2011 to other political parties to come together, the formulation of these United Struggle bodies is another unprecedented momentum for the anti-Woyane Struggle that is already ongoing.

From the perspective of this historical epoch of time in which our country is in, the situation will force us to be in coalition than in disintegration; and to stick together than get separated.

Tila Magazine exclusively believes that scattered political stand and struggle is highly exposed to the TPLF's "divide and conquer" strategy; so it is compulsory to come under nation-wide visionary, all-inclusive and community based umbrella of struggle.

So we would like to send a clear and loud message to those who are still in dispersion to scrutinize their way and would rather focus on all-inclusive national vision than trivial and myopic goals; and to give emphasis on peoples' sustainable interest than self and party interest. **Tila Magazine** brings you as always new faces and ideas, opportunities and a special guest of honor. Have a nice reading!!!

``**Tila Magazine** is yours Magazine! **Tila** is a Magazine not only you read it,but also you will write on it!``



# ርዕሰ አንቀጽ

## ፍፃሜው ታላቅ ይሆናል!

እንደሚታወቀው ከዚህ በፊት በወጡ የጥላ መጽሄት እትሞቻችን ላይ በተበታተነ ሁኔታ የሚንቀሳቀሱ የተቃውሞ ጎራ ሃይሎች ለአንድ አላማና ግብ በህብረት መታገል እንዳለባቸው ስናሳስብ መቆየታችን ይታወሳል።

በመሆኑም ይህን ሃሳብ በሚያጎለብት መልኩ ባሳለፍናቸው ሶስት ወራት የኢትዮጵያ ብሄራዊ የሽግግር ምክር ቤትና  የኢትዮጵያ ህዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ(ሸንጎ)ተመስርተዋል።




የእነዚህ ህብረቶች ተቀዳሚ አላማም በተበታተነ ሁኔታ የሚገኙ የፖለቲካ ሃይሎችን በማሰባሰብ ሁሉን አቀፍ የሆነ የሽግግር መንግስት እንዲቋቋም ሁኔታዎችን ማመቻቸት ነው።

በእርግጥ በነጀነራል ከማል ገልቹ የሚመራው የኦሮሞ ነፃነት ግንባር በዲሴምበር 2011 ላይ የፓርቲውን የፖለቲካ ፕሮግራም በማሻሻል ሌሎች የተቃዋሚ ሃይሎች በአንድነት እንዲሰለፉ ያደረገውን ጥሪ ተከትሎ የእነዚህ ህብረቶች መቋቋም እየተካሄደ ላለው ፀረ-ወያኔ ህዝባዊ ትግል የሚያበረክተው አስተዋፅኦ ቀላል የሚባል አይደለም።

በመሆኑም ሃገራችን ካለችበት ወሳኝ የታሪክ ምዕራፍ አኳያ ከመበታተን ይልቅ መዋሃድን፤ ከመለያየት ይልቅ መቀራረብን እንድናስቀድም ያለንበት ሁኔታ ግድ ይለናል።

በተለይም የተበታተነ የፖለቲካ አቋም ትግል  የወያኔ አገዛዝ ነጣጥሎ ለመምታት በየጊዜው ለሚጠቀምበት ሥልት የተጋለጠ  በመሆኑ አንድ ሀገራዊ ራዕይ ያለው ሁሉን አቀፍ የሆነ እና ህዝባዊ መሠረት ያለው ጠንካራ ኃይል እንደሚያስፈልግ የጥላ መፅሄት እምነት ነው።

ስለሆነም አሁንም በተበታተነ አኳኋን እየተጓዙ የሚገኙ አካላት ቆም ብለው መንገዳቸውን እንዲፈትሹ፤ከቁንፅል ግብ ይልቅ ሁሉን ያማከለ ሃገራዊ ራዕይን ከድርጅታዊ ጥቅመኝነት ይልቅ የህዝብን ዘለቄታዊ ጥቅም በሚያስቀድም ሃገራዊ አንድነት ላይ እንዲያተኩሩ ለማሳሰብ እንወዳለን። ጥላ መፅሄት እንደተለመደው አዳዲስ ፊቶችንና ሃሳቦችን፤ዕድሎችንና ልዩ የክብር እንግዶችን ይዛ ባላችሁበት ደርሳለች።መልካም ንባብ ተሳትፎአችሁ አይለየን-የእኛ መልዕክት ነው!

"**ጥላ** መፅሄት የእናንተው መፅሄት ናት! **ጥላ** የሚያነቧት ብቻ ሳትሆን የሚፅፉባትም መፅሄት ናት"

# About Tila
# Dear Readers

Realizing the fact that the digital age has empowered and made ordinary people across the world irrepressible beyond their imagination, **WE** aims to serve as a credible platform that will spread uncensored interviews, news, commentaries and analyses that are unlikely to see daylight in Ethiopia.

Fortunately, here is where you find **TILA**, the un-disputably best source of information serving the Ethiopian Diaspora community in Europe & America with a proven record of excellence in journalism.

**TILA** is a political magazine, published and distributed by patriotic Ethiopians around Hessen region in Germany, which appears in Amharic, English and Germany Languages every 3 months. It is a magazine of quality, responsibility and standard. Entertainment and sport are among our coverage issues next to Ethiopian politics.

As a reader, you are to get useful political and current news in **TILA** than any other publication can offer you. More comprehensive analysis and interpretations than any other media can present to you. In fact, these are some of the qualities of **TILA** that has made it the largest circulating magazine in its category. TILA magazine has also partnered with ethiomedia.com, ethiogermany.de and afroaddis.wordpress.com among others, to deliver reliable and high quality content to our visitors.

Don't take the chance of missing this spectacular political magazine. Subscribe to it today!

We promise, you won't regret your decision. Reach us on tilamagazine@yahoo.de & tilamagazine.yolasite.com

**Tila Magazine is yours Magazine!**

# ከአዘጋጆች
# ውድ አንባብያን

ጥላ መፅሄት በየሶስት ወሩ የሚታተም የፖለቲካ መፅሄት ነው።መፅሄቱ የኢትዮጵያን ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ መሰረት አድርጎ በጀርመን አገር የሚታተም ቢሆንም መረጃ መረቦችን በመጠቀም መላውን ዓለም የማዳረስ ዓላማን አንግቦ እየተንቀሳቀሰ ነው።

የአገራችንን ወቅታዊ ሁኔታና ጠቃሚ መረጃዎችን በማካተት ዝናን ያተረፈው የጥምረት መፅሄት አዘጋጆች ያቋቋሙት ጥላ መፅሄት የስሙ ስያሜ እንደሚያመለክተው የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ሃይሎች በተበታተነ ሁኔታ የሚያካሂዱትን የትግል ሂደት በማስቀረት በአንድ **ጥላ** ስር እንዲሰባሰቡ ለማሳሰብና አቅጣጫ ለመጠቆም ነው።

የፖለቲካ ሃይሎች በተበታተነ ትግላቸው ጋት እንኳን መራመድ እንደማይችሉ በመገንዘብ የጋራ ትግል እንዲያካሂዱ ለማበረታታትም ጭምር ነው እ.ኤ.አ ከጥር 2012 ጀምሮ በዚህ ስም መፅሄቱ እንዲጠራ የወሰንነው።በመፅሄቱ አዝናኝና አስተማሪ ዝግጅቶች የሚካተቱበት ሲሆን ስፖርትም ትኩረት ያገኛል።

ጥላ መፅሄት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ሃሳቡን ያለምንም ገደብ በነፃነት የሚያቀርብበት ክፍት መድረክ በመሆኑ በመፅሄቱ የሚወጡት ፅሁፎች በሙሉ የፀሃፊዎቹን እንጂ የጥላ መፅሄት ዝግጅት ክፍልን የማይመለከቱ መሆናቸውንም መግለፅ እንወዳለን።

**ጥላ መፅሄት የእናንተው መፅሄት ነው!**

## Current Affairs

# The Sugar Candy Mountain

**Dawit Fanta (Engineer)/Germany**

In George Orwell's book called "Animal Farm", there is a most intriguing character named Moses. It is a tame raven and typically characterized by its attribute of preaching about the intangible hope of a Sugar Candy Mountain where it was Sunday seven days a week, clover was in season all the year round, and lump sugar and linseed cake grew on the hedges. It was just an illusory hope to deceive other animals.

In this very nature of trait, the raven Moses and the dictator Zenawi have a common feature except that Zenawi couldn't be tamed unlike Moses did in that he rules the country by the law of the jungle rather than the rule of law for the last twenty one years.

As a replica story of Moses, Zenawi is a dared evil in talking about the intangible fairyland where:

- Its citizens would be fed three times a day; but what we have seen for the last twenty one years is against his illusory nightmare. At least the number of starved people is increasing exponentially year after year.
- He claimed as if Ethiopia had acquired a Two-Digit Economic growth for the last six consecutive years. But keep in mind that this figure hasn't ever been approved by the international report; rather it is against the World Bank report.

He claimed that Ethiopia would be in the same status as those countries which are in mid level GDP in his 15 years development plan. But according to the 2011 Legatum Prosperity Index, Ethiopia is still in the penultimate row which is 108$^{th}$ out of 110 countries *(The 2011 Legatum Prosperity Index Page 3)*. So how long does Zenawi need else than twenty one solid years to show us the creation of fairyland (his version of Sugar Candy Mountain)?

Irrespective of his rhetoric bluff, Ethiopia is at the brink of cataclysmic crisis both economically and politically. For today, let's see a single cord of economic crisis Ethiopia faced because of the wrong policy of the Zenawi regime.

### The Incurable Wound

Since early 2007 up to now, Ethiopia has faced a non-stoppable and rampant inflation rate. And Zenawi is trying to bamboozle us by claiming that the causes of the soaring inflation rate are a growing economy, an increase in demand (which means it is a demand-pull inflation) and farmers are trying to demand higher price for their product.

But anyone like me who took at least baby Economics 101 can confidently challenge his idiotic explanation.

a. If the soaring inflation rate is caused by a growing economy and an increased de-

mand, then there would be a sign of reduction in an unemployment rate. But, as never seen ever before, the unemployment rate is extremely high. It becomes common to see countless jobless Tertiary School graduates, people who are wandering in search of job in vain, a bunch of beggars in 50 meters distance over the street of cities and most sadly to see child prostitution in every corner of major cities to get money for subsistence. So, can one say that the above entire terrible socio-economic crisis is a sign of growth in economy?

If farmers are asking higher price for their agricultural outputs, this higher price must make them to produce more and supply more to the market. So there would be increase in supply and reduce the price. As a basic concept of Demand-Supply curve, the higher outputs must increase in demand will be balanced by the increase in supply then there will not be a significant price change. But what we are looking in Ethiopia is completely different. So there must be other reasons for this rampant inflation rate.

Although there are so many external factors that contribute for inflation rate like the soaring oil price and World Bank requirements of SAP (Structural Adjustment Programme) I would like to focus on the direct role of TPLF led ruling party in causing this rampant inflation rate.

## Quid Pro Quo

By its dictionary definition "Quid pro quo" does mean that something that is given to a person in return for something they have done.

On 2010 EPRDF officially declared that it has five million cadres all over the country. And it is very obvious that most of them are "Purchased Cadres" who preach the "holiness" of EPRDF in every level of society and in return the Zenawi regime flooded them in cash to guarantee their loyalty; which means government's expenditure on these cadres is extremely huge so the government prints more money to finance its budget deficit through the creation of money. So, such an increase in money supply leads to the situation of "too many Birr (the Ethiopia Currency) chasing too few goods"; which seriously resulting in high inflation rate.

## The Financial Sabotage of TPLF

The following are facts-on-ground in Ethiopia:

a. Interest rate is extremely low

b. Inflation rate is extremely high

TPLF owned Trade Empire named EFFORT,TIRET of Amhara National Democratic Movement (ANDM),WONDO of The Southern Ethiopian People Democratic Movement (SEPDM) and DINSHO of Oromo People Democratic Organaization(OPDO) are the sole favoured institutions which had borrowed in billions of Birr from state owned banks with nil requirements.

Keeping the above facts into consideration, during a situation of low interest rate and high inflation rate the adjusted interest rate for inflation will be negative; which means the negative real interest rate redistribute the income and asset from savers to borrowers unfairly.

So that it is a financial sabotage of TPLF/EPRDF to make its institutions advantageous over this unfair payoff at a cost of millions of innocent Ethiopian life.

# ትናንትና ዛሬ

Dawit Muse /Münnerstadt

ሕወሃት ወያኔ በትጥቅ ትግሉ ዘመን በበረሃና ዋሻ ሣለ ከሙስሊሙ አረብ ሃገራት እንዲሁም ከሌሎች ተባባሪዎች ኢትዮጵያ የሙስሊም ሃገር ናት በማለት የመሣሪያ የገንዘብና የሎጂስቲክ ስጦታና እርዳታ መነገዱንና ማካበቱን ረጂዎቹም እኛም ኢትዮጵያውን የምናውቀው እውነት ነው:: ታዲያ በቆሻሻ የንግድ ስትራቴጂው በአንጻሩ መስጊድ በቤተክርስቲያን ቤተክርስትያን በመስጊድ ላይ አልዘሙተም::

ይሁንና የታሪክ አጋጣሚ ሆኖ በለስ ቢቀናውም ዛሬም በመሃል ሃገር ቤተመንግስት ውስጥና ባማሩ የከተማ አፓርታማዎች ተቀምጦ ጫካ ይመራበት በነበረ ሕገ አራዊት አስተሣሠብ ዳግም ሕዝቡን በሃይማኖት በዘር በክልልና መንደር አልበጣጠስ አልጠፋ ብሎ ሲለው አሸባሪነት /ቴረሪስት/ በማለት ዴሞክራት ተቃዋሚ ድርጅቶችን ከማሳደድና ከመግደል አልቦዘነም:: አንዴ በሶማሌ የውስጥ ጉዳይ አንዴ በሱዳን የውስጥ አጀንዳ እንዲሁም ከኤርትራ የሌብነት የዘርፍያ ግጭት በመተናኮስ ከምራባውያን አገራት ወይም ከአሜሪካና አውሮፓ በአሸባሪነት መከላከል ስም እነሆ ትላንት በስልምና ዛሬ ደግሞ ከክርስቲያን ሃገሮች መሣሪያ የገንዘብ ስጦታና እርዳታ ሲያግበሰብስ እየተመለከትን ነው::

ይሁንና ወያኔ ዘላቂ ጥቅም እንጂ ዘላቂ ወዳጅነት እንደሌለው ስንቶቻችን ስልጣን ላይ ባቆናጠጣቸውና ማእረግ በጫነላቸው ላይ ሲንሸራተት አይተነው ይሆን:: ቢሆንም በወያኔ የተደናበረ አመራርና አገዛዝ በአንጻሩ በሃይማኖት በዘር በመንደር ተነድቶ ቢሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ ዛሬ በሀገራች ውስጥ ቀድሞ በተኮሰና በጣለ የሚኖርባት ሃገር ትኖረን ነበር አልሆነም::

አሁንማ ይህው በየሰአቱ የአንዱ እምነት ተከታይ የሌላውን በፍረሃትና በጠላትነት እየተመለከተ የሰው ልጆች በፈንጂና በሮኬት እየተበጫጨቁ ዘግናኝ ትዕይንት ተመልካቾች ሆነናል:: ታዲያ ምስራቅ አፍሪካን የሚከታተሉ የምእራቡ አለም ፖለቲካ ተንታኞች ሌላው ዓለም ከኢትዮጵያ የሃይማኖትና የዘር ተከባብሮ ተቻችሎ መኖር መገንዘብ መረዳት እንዳለበት ይመከራሉ:: ይሁን እንጂ ወያኔ ሕወሃት እቅዱ ሃገራችን ባልዋት 81 ብሄረሰቦችዋ ቁጥር የተበጣጠሰች ደሴት ፈጥሮ በሠራቸው ደሴቶች ውስጥ እየተሽሎከለከ ታጣቂ የባሕር ዘራፊ ሆኖ ለመኖር መሆኑን እቅዱን ተረድተን ልናከሽፍበት የታሪክና የትውልድ ግዴታ አለብን::ኢትዮጵያን እግዚአብሄር ይባርክ!

# ቢቃ!!!

Minewar Abdulwahid Kemal /Hof

ላለፉት 21 ዓመታት በሥልጣን የቆየው የወያኔ መንግስት በሃገራችንና ህዝቦቿ ላይ እያስከተለ ያለው ጉዳት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየከፋ ይገኛል:: ከነዚህም መካከል ሃገራችን በዘረኝነት ከመከፋፈሏ ባሻገር ህዝቦቿ ማህበራዊም ሆነ ኢኮኖሚያዊ ፍትህ በማጣት በከፍተኛ ችግር ውስጥ ይገኛሉ:: ስለሆነም ወያኔ በስልጣን እስካለ ለዜጎቻችንም ሆነ ለሃገራችን የተሻለ ነገር ሊመጣ አይችልም::ስለዚህ በተባበረ ክንዳችን ወያኔን ቢቃ ልንለው ይገባል::

# ያልተሳካው የተቋማት ግንባታ

Tariku Abate /Hof

የወያኔው መንግስት ምንም እንኳን ለሁለት ዐስርት አመታት በስልጣን ቢቆይም ህዝባዊ ተቋማትን ከመገንባት ይልቅ ለራሱ እየተገለገለባቸዉ ይገኛል። ለምሳሌ የሃገሪቱ መከላከያ ሰራዊት የደህንነቱ መስሪያ ቤት እንዲሁም ፍርድ ቤቶች ህዝብን ከማገልገል ይልቅ የወያኔ የፖለቲካ ማስፈጸሚያ ሆነዋል።እንዲሁም እነዚህ መስሪያ ቤቶች ታማኝነታቸው ለህዝብ እና ለህገ መንግስቱ ባለመሆኑ ዜጎቻችን ፍትህ በማጣት በጭቆና ቀምበር ስር እንዲኖሩ አስገድዷቸዋል። በመሆኑም የጭቆናን ቀንበር ለመሰባበር እና ለህዝብ ታማኝ የሆኑ ተቋማትን ለመገንባት የወያኔን መንግስት ልናስወግደው ይገባል።

# የሃይማኖት ነጻነት ይከበር!!!

Tadess Alemu/Hof

ምንም እንኳ የወያኔ መንግስት በህገ_መንግስቱ የሃይማኖት ነጻነትን አውጃለሁ ቢልም በተግባር እየታየ ያለው ግን መንግስት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ ከመግባቱም ባሻገር የሃይማኖት አባቶችን በማሰርና በማሰቃየት ዜጎች እምነታቸውን በነጻነት እንዳይከተሉ በማድረግ ላይ ይገኛል።

በተጨማሪም የ ወያኔ መንግስት የረጅም ጊዜ ታሪክ ያላቸውን የአምልኮ ስፍራዎችን እና የሃገራችንን ቅርሶች በልማት ስም እያጠፋ ይገኛል።

ስለሆነም የሃይማኖት ነጻነት የሚከበርባት፣ታሪካዊ ቅርሶቻችን ተጠብቀው የሚኖሩባት፣ እንዲሁም ሃሳብን በነጻነት መግለጽ የሚቻልባትን አንዲት ኢትዮጵያን ለመገንባት እንቅፋት የሆነውን የወያኔ መንግስት ለማስወገድ በጋራ እንታገል።

# የካንጋሮው ፍርድ ቤት ውሎ

Yohannes Selamu /Hof

በእርግጥም ልማዳዊ እና የህግ የበላይነት ያልሰፈነበት ችሎት በአሜሪካኖች አባባል የካንጋሮ ፍርድ ቤት ይባላል። እናም

የወያኔው የካንጋሮ ፍርድ ቤት በ July 13, 2012, በዋለው "ችሎት" በሃገር ውስጥ እና በውጭ የሚገኙ ጋዜጠኞችን፤የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅት አመራሮችን እንዲሁም አክቲቪስቶችን "በሽብርተኝነት ወንጀል" ከ 8 ዓመት እስከ ዕድሜ ልክ እስር ፈርዶባቸዋል። ከነዚህም መካከል በቅርቡ በጀርመን ሃገር ኑረንበርግ ከተማ በፌብሯሪ 18, 2012 በተደረገው ስብሰባ ላይ ተጋባዥ እንግዳ የነበሩት አቶ አባንግ ሜቶ / በሌሉበት የ18 ዓመት ጽኑ እስራት የተፈረደባቸው/ ይገኙበታል።

የፍርድ ሁኔታውን አጠቃላይ ሁኔታ ስንመለከት የወያኔ መንግስት እንደአቋም ሃሳብን በነጻነት መግለጽን፤ለሰብዐዊ መብት እና ክብር ተሟጋች ሆኖ መቅረብን እንዲሁም አማራጭ የፖለቲካ አመለካከት መያዝን እንደወንጀል በመቁጠር ላይ ይገኛል። ይህም የሚያመለክተው የወያኔ መንግስት ከዴሞክራሲያዊ አስተዳደር ይልቅ አሃዳዊ ሥርዐትን፤ ከሰብዐዊ መብት እና ክብር ይልቅ ለሥርዐቱ ማንብደድን በዋናነት እያራመደ መሆኑን ያመለክታል።ከዚህም ባሻገር የወያኔ አስተዳደር ፍርድቤቶችን ለእኩይ ዓላማው ማስፈጸሚያ እየተገለገለባቸው ይገኛል።

በመሆኑም ፍትህን ከወያኔ ካንጋሮ ፍርድቤቶች ማግኘት እንደማይቻል ማረጋገጥ ችለናል። ስለሆነም የህግ የበላይነት የሚከበርባት፤የዜጎች ሰብዐዊ ክብር የሚረጋገጥባት አንዲት ኢትዮጵያን ለመገንባት በጋራ እንነሳ።

# የግፍ ዘመን ይብቃ

**Abebe Demelash /Hof**

ላለፉት ሁለት አስርት ዓመታት ወያኔ በህዝባችን ላይ የተለያዩ በደሎችን እያደረሰ ይገኛል። ይህም አልበቃ ብሎ በሃሰተኛ ውንጀላ በሃገር ውስጥ እና በውጭ የሚገኙ የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ አመራሮችን፤የሰብዐዊ መብት ተከራካሪዎችን እና ጋዜጠኞችን በማሰርና በመወንጀል ይገኛል። ከዚህም ባሻገር የህዝባችንን ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብቶችን ሙሉ በሙሉ ለመገደብ ሲባል የተለያዩ አፋኝ ህጎችን በስራ ላይ ከማዋሉም ባሻገር በግል ጋዜጦች ላይ ቅድመ-ህትመት ምርመራ /Censorship/ እንዲደረግ በማስገደድ ላይ ይገኛል።

በተጨማሪም በመላ ሃገሪቱ የሚገኙ ወጣቶችን የኢህአዴግ የወጣቶች ሊግ አባል ካልሆኑ በተማሩበትም ሆነ በሰለጠኑበት የሙያ ዘርፍ ስራ ማግኘት እንዳይችሉ በማድረግ ዜጎች በሃገራቸው ላይ እንደ ሁለተኛ ዜጋ ራሳቸውን እንዲቆጥሩ በማድረግ ሃገሪቱ ከመቼውም ጊዜ በላይ ከፍተኛ በሆነ የስራ አጥ ቁጥር እንድትሞላ አድርጓታል።

በሌላ በኩል በወያኔ የተሳሳተ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ምክንያት የሃገራችን ህዝብ ሊቋቋመው ከሚችለው በላይ ከፍተኛ የሚባል የዋጋ ግሽበት የተከሰተ በመሆኑ ከጥቂት የወያኔ ስርዐት ጥቅመኞች ውጭ መላው የሃገሪቱ ህዝብ የዚሁ የተሳሳተ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ሰለባ ሆኗል። በመሆኑም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአረቡ አለም ማለትም በቱኒዚያ፤ በግብጽ፤ በሊቢያ እና ሶሪያ እንደታየው በህዝብ እንባ ላይ የሚነግደውን የወያኔ መንግስት በተባበረ ሃይላችን ልንጥለው ይገባል።ስለዚህም ህዝባችንን ከጥፋት፤ሃገራችንንም ከመፈራረስ ለመታደግ የፖለቲካ ልዩነቶቻችንን ወደጎን በመተው በጋራ ጠላታችን ወያኔ ላይ ልንዘምት ይገባል።

# የዕድገት ማነቆ

**Samuel Demere /Nürnberg**

የገዥው የወያኔ ህወሃት አመራሮች መላው ሃገራችንን ጠቅልሎ ለመግዛት ያላቸውን ብርቱ ፍላጎት እውን ለማድረግ ሰሞኑን ያወጡትን አዋጅ መላው ኢትዮጵያውያን ዝም ሊለው የሚገባ ጉዳይ አይደለም።

ይኸውም በኢንተርኔት አማካኝነት በድምጽ፣በምስል እና በጽሁፍ የሚተላለፉ መልዕክቶችን ማገድ እና የሰውን የአስተሳሰብ መንፈስ የስራ ተነሳሽነቱንና የዴሞክራሲ እና የሰብዐዊ መብቱን ማፈንና ማውደም ነው።

ባለንበት ክፍለ ዘመን ማለትም በ21ኛው ክፍለ ዘመን በኢንተርኔት፤በኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ፤ በመረጃ፤ በስነ-ጽሁፍ፤ በፈጣን መረጃ ምሳሌ በሆኑት አገራችን ኢትዮጵያ የመጨረሻ ደረጃ የያዘች ውራ ሆነናል ይህም በጣም የሚያሳፍርና የሚያሳዝን ነው።

እንደሚታወቀው የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን አገልግሎት ለኢትዮጵያ በቀላሉና በውጪ ያለውን የኢኮኖሚ ዕድገትና የተለያዩ ጠቃሚ የሆኑ እውቀቶችን የምንቀስምበት አንዱ እና ዋነኛው ነው።ከነዚህም ዋና ዋናዎቹ የርቀት ትምህርት፤ለንግድ እና ለቁጠባ ትምህርት፤ በቀላሉ በቤታችን ሆነን የተለያዩ እውቀቶችን የምናዳብርበት ነው።ሃገራችን ኢትዮጵያ ለዚህ አልታደለችም።

ወያኔዎች በዚህ የሚያበቁ አይደሉም።አገሪቷን ከዝርፊያና ህዝቡን በጠመንጃ ለማፈን እና ለማውደም ቆርጠው ተነስተዋል።እያንዳንዱን እንቅስቃሴ ከራሳቸው ጥቅም አኳያ የሚያዩትየወያኔ ህወሃት መሪዎች ስልጣናቸውን ለማረጋጋትና ለማራዘም ካላቸው ብርቱ ፍላጎት አገራችንን (ህዝባችንን) ወደ አዘቅት ውስጥ ጨምረውታል።አገዛዙ ኢህአዴግ ለስልጣን ማስረዘም ማነቆ ይሆናሉ በለው የሚያስቧቸው የግል ጋዜጣ፤ሬድዮ እና የቴሌቪዥን ስርጭቶችን ለማፈንና ለፍትህ፤ ለዴሞክራሲ፤ ለነጻነት የሚታገሉ ሃይሎችን በቅርብ ለመከታተልና (ለመሰለል) የሚጠቀሙበት ስልት ነው።ሌላው የኢትዮጵያ ቴሌ ኮሚኒኬሽን ኩባንያን እንደራሳቸው ንብረት የሚጠቀሙበት ኩባንያ ከሆነ

ውሎ ሰንበቷል፡፡ሃገራችን በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እጅግ አሳሳቢ ነው በተለይም ከሰሞኑ የወጣው አዋጅ የዕድገት ማነቆ የዜጎችን የመናገር፤የማወቅ፤የመወያየት መብትን የሚገድብ አዋጅ ነው፡፡

ስለዚህ ይህ አዋጅ የፀረ-ሽብር ህግ ተብሎ ከሚጠራው ጋዜጠኞችን እና የፖለቲካ መሪዎችን እና ደጋፊዎችን መቀመቅ ከሚከተው አዋጅ የሚተናነስ አይደለም፡፡ህግ፤መንግስት፤ፍርድቤት የእምነት ቦታዎችን ጨምሮ ጣልቃ በመግባት አገራችንን እንዴት ወደ አስከፊ ሁኔታ እንደገባች የተደበቀ ምስጢር አይደለም፡፡

የኢትዮጵያ ህዝብ ግን በእንደዚህ አይነቱ በልጆች ጨዋታ የሚደናገጥ አይደለም፡፡ፈጣሪ ያደለውን የተፈጥሮ መብት ማገድ አይቻልም፡፡ እና ወገኖቼ ይህንን የእድገት ማነቆ ለመላቀቅ በአንድነት እንነሳ እላለው፡፡

# መፍትሔ ያጣው የዜጎቻችን ስቃይ

**Betelhem Weledemichael/ Hannover**

ምንም እንኳን የወያኔ መንግስት ከፍተኛ የሆነ የኢኮኖሚ ዕድገት እያስመዘገበኩ ነው ቢልም በተግባር ግን እየታየ ያለው ዜጎች ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ፍትህ በማጣት ከመሰቃየታቸውም በላይ በአሁኑ ወቅት ከዚህ የጭቆና ቀንበር ለመላቀቅ በተለይ የነገ የሃገሪቱ ተስፋ  ይሆናሉ የሚባሉት ወጣቶች ለህይወታቸው እጅግ አደገኛ በሆነ ሁኔታ እየተሰደዱ ይገኛል፡፡ ለምሳሌ በ2012 ብቻ በግፍ በአሰሪዎቿ እየተደበደበች ህይወቷ ያለፈው ዓለም ደቻሳ፣ በኮንቴይነር ተጭነው ወደ ደቡብ አፍሪካ ሲጓዙ የነበሩ ነገር ግን በአየር ማጣት ምክንያት ታፍነው በታንዛኒያ በረሃ የቀሩት 42 ኢትዮጵያውያን ሞት እንዲሁም በተመሳሳይ ወደ ደቡብ አፍሪካ በባህር ሲጓዙ ጀልባቸው ሰጥማ በማላዊ የሞቱት 48 ኢትዮጵያውያን ሞት ለአብነት የሚጠቀስ ነው፡፡

የወያኔ ኮሚኒስታዊ ርዝራዥ የሆነው "የአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ" ፍልስፍና  በሃገራችን እያስከተለ ያለው ችግር በዚህ ሳይወሰን የዜጎችን የመናገር እና ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብትን በማፈን፤ጋዜጠኞችን በሃሰት ክስ በማሰርና በማሰቃየት፣ እንዲሁም ነፃ ጋዜጦችን ቅድመ-ህትመት ምርመራ እንዲያደርጉ በማስገደድ የዜጎቻችንን ሰብዐዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በሃይል በመጨፍለቅ ላይ ይገኛል፡፡

በተጨማሪም ስርዓቱ ለመድብለ ፓርቲ መስፋፋት ዕንቅፋት የሆኑ ህጎችን በየጊዜው ስለሚያወጣ የአንድ ፓርቲ የበላይነት የነገሰበት የፖለቲካ ምህዳር እንዲፈጠር ምክንያት ሆኗል፡፡

ስለሆነም ይህን ለሃገራችን እና ለህዝቦቿ ነፃነት ዕንቅፋት የሆነውን የወያኔ መንግስት በተባበረ ክንዳችን ልናስወግደው ይገባል፡፡

# በጋራ እንነሳ

**Tigist Alebachew/Bayreuth**

የአንድ አገር መሰረቱ ህዝብ ነው ህዝቡ ደግሞ ከመኖሪያ ቀዬው እየተፈናቀለ ከወጣ መንግስት ማንን ሊመራ ነው?የወያኔ መንግስት የኢትዮጵያን ህዝብ ለስደት እየዳረገው ነው ያለው ስለዚህ መልካም አስተዳደር ከሌለው ሰላም የለም፡፡ሰላም ከሌለ ሁሉም የለም፡፡ስለሆነም የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ በጋራ እንነሳ እንወያይ አንድ በመሆንም አምባገነኑን የወያኔ መንግስት ከስልያኑ እናስወግደው!

# ግዛኝ ግዛኝ ብለው ለመሸጥ አሰበኝ

**Gashaw Melese/Bayreuth**

የኢትዮጵያ ህዝብ በሃገሩና በቀየው ካልኖረ እስላም ክርስቲያኑ መኖሪያ ካጣ ገዳማት መስጊዱ ከተዘጉ መነኮሳት እየተፈናቀሉ ፤ህዝብን በእስራትና በማፈናቀል የሚመጣ ዕድገት ለማንም ግራ የሚያጋባ ነው፡፡ወያኔ የራሱን ስልጣን ለማራዘም ስለ እድገትና ልማት ቢያወራም አባቶቻችን ያቆዩትን መሬት እየሸጠ ከወግና ከባህሉ ለማውጣት የሚያደርገውን ጥረት ልናስወግደው ይገባል፡፡ይህንን ስርዓት አልባ መንግስት በዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለመተካት ሁላችንም የበኩላችንን እንወጣ!

# ሰፊው ህዝብ ያሸንፋል!

**Trsit Haile/Bayreuth**

ኢትዮጵያ የነጻነት ምሳሌ እንዳልነበረች ዛሬ በጥቂት አምባገነኖች ቅርፅዋንና ክብሯን አጥታ ዜጎቿ በአገር ውስጥ ለአምባገነኖቹ እስራትና ግርፋት ሞት ሲቀበሉ በውጭ አገር ያሉትም በስደት ምክንያት ለእንግልትና ለውርደት ተዳርገዋል፡፡ጎበዝ እንደቀደሙት አባቶች ዘመናዊ ጦር መሳሪያ በማየት እንዳልሸሹቱ ይልቁንም እምቢ በማለት በአቅማቸው ታግለው እንዳሸነፉትና የአገራችንን ክብር እንዳስጠበቁት አርበኞች እኛም እንደወረስነው ክብር የአርበኝነት ታሪክ መድገም ያለብን ዛሬ ነው!! ሰፊው ህዝብ ሁሌም ቢሆን ያሸንፋል!!

# የኢትዮጵያ ህዝብና የአምባገነኑ ቡድን ፍጥጫ

**Dagmawi Yeshitla/Treysa**

በአሁኑ ሰዓት የኢትዮጵያ ህዝብ ከመቼውም በበለጠ በችግርና እንግልት ላይ ነው፡፡ ችግሩም በጣም አሳሳቢ ከመሆኑ የተነሳ በተለያዩ የዜና እወጃዎችና በአለም የሰብዓዊ መብት

ተሚጋቾች ሪፖርት ላይ ሁሌ የሚነገር የዘወትር ተግባር ሆኗል።

ሰዎች ይገደላሉ ይታሰራሉ በፀጥታ ሃይሎች ታፍነው ወዴት እንደሚደርሱ የማይታወቅበት ሁኔታ እንዳለ ሳይቀር የሚዘገቡ አበይት ጉዳዮች ሆነዋል።ይህን ማየት የኢትዮጵያ ህዝብ የዕለት ከዕለት ትእይንት መሆኑን ከማስገረምም አልፎ አሁን ህዝቡ አምቆ የያዘውን ትዕግስትና አላስፈላጊ የሆነ በህዝብ ላይ የሚደርሰው ደም ማፍሰስ እንዳይኖር ከማሰብ ጋር ተያይዞ ዛሬ ለሙብቱና ለነፃነቱ ለመታገል ሰላማዊ ትግልና የህዝብ አመፅን ለመጀመር በቋፍ ላይ ይገኛል።ምናልባትም የኢትዮጵያ ህዝብ የነፃነት ጊዜ አሁን ሰዓቱ እየደረሰ መሆኑን የሚያሳይ ምልክቶች እየታዩ መሆኑን ህዝቡ በዚህ አደገኛና ዘራፊ ወንጀለኛ ቡድን ወያኔ ላይ የተባበረ ህዝባዊ ተቃውሞ ማድረግ ከጀመረ ውሎ አድሯል።

ይህንንም ትግል አይቶ የህዝብ ስነልቦና ለመስረቅ ከላይ ታች የሚለው ይህ አደገኛ ቡድን ህዝቡን የተዛባ አስተያየት እንዲኖረው የማይሆንና በማንኛውም ህዝብ ሃሳብ ውስጥ የሌለ አመለካከት እንዲሰርፅና ህዝቡም ሁሌ ይሄንን የወያኔ ቡድን ይግዛን ብሎ እንዲያስብ በማድረግ የፕሮፓጋንዳ ዘመቻውን እያጧጧፈ ይገኛል።

የኢትዮጵያ ህዝብ ለወደፊቱ ምን እንደሚመጣ ጠንቅቆ የሚያውቅና ከዚህ አደገኛ ቡድን የበለጠ ቀድሞ የሚያስብ ህዝብ እንደሆነ መረዳት ይቻላል።ይህም ይሄ አደገኛ የህዝብ ፀር የሆነ መንግስት ከቻለ በደንብ እየረገጠ እየገደለና እያሰረ ህዝብን ማኖር፤ ካልቻለ ደግሞ ህዝብና ህዝብ አጋጭቶና አናክሶ የዘረፈውን የህዝብ ሃብትን ጭኖ ለመጥፋት የተዘጋጀ ሃይል መሆኑ ዛሬ ሳይሆን ስልጣን ከመቆናጠጡ በፊት የኢትዮጵያ ህዝብ ያቀዋል።

ዛሬ የሚፈጥራቸው መጥፎ ሃሳቦች ሁሉ በህዝቡ ተቀባይነት የለውም እናም ኢትዮጵያውያን አሁንም ቢሆን የሚያደርገውን ተቃውሞና ይህን አደገኛ ቡድን ካንቀላፋበት የስልጣን ወንበር ለመገርሰስ ስልታዊና የበሰለ አስተሳሰብ በማሰብ ለትውልድ በማሰብም ጭምር ትግሉን መቀጠል አለበት።ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!

# እሳት ከሌለ ጭስ አይኖርም

**Michael Melaku /Bayreuth**

ከዓለም ህዝቦች ታሪክ መማር ከተፈለገ በዘመናት አምባገነኖችን ከስልጣናቸው የሚወርዱት በህዝብ መራራ አመፅ ባልተቋረጠ ትግል መሆኑን ማንም የሚያውቀው ጉዳይ ነው።በደል ግፍ ስቃይ መከራ ጭቆና ይሁን ፍትህ መጓደል ሲኖር ሰብዓዊ ፍጡር ቀርቶ እንስሳትም ማመፃቸው የተፈጥሮ ህግ ነው።እሳት ከሌለ ጭስ አይኖርም እንደሚባለው በደልና ግፍ ከሌለ አመፅ ሊኖር አይችልም።

በመሆኑም የአመፅ ሁሉ ምንጩና ምክንያቱ በደልና ጭቆና ነው።አረመኔያዊ አምባገነኑ የወያኔ መንግስት የኢትዮጵያን ህዝብ በጎሳ ፖለቲካው መምራት ከጀመረ 21 ዓመታት ተቆጥረዋል።በ21 ዓመታት ውስጥ ስፍር ቁጥር የሌላቸው በደሎች በዜጎች ላይ ተፈፅመዋል።እየተፈፀመም ነው።የኢትዮጵያ ህዝብ ተቻችሎና ተከባብሮ የሚኖር ህዝብ ቢሆንም ህዝብን ከህዝብ ማጋጨት እንዲሁም በሃይማኖት ውስጥ ጣልቃ እየገባ ህዝቡን መከፋፈልና አገሪቱን ወደ አስከፊ ጎዳና እየመራት ይረገኛል።

በቅርቡ እንኳን ከ800 ዓመታት በላይ እድሜ ያለው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የዋልድባ ገዳምን ለስኳር ፋብሪካ በሚል ካልጠፈዳ ቦታ ህዝቡን በመናቅ የገዳም መነኮሳትን በመደብደብና በማሰር ላይ የሚገኝ ሲሆን በውጭ አገር በስደት የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ድርጊቱን በመቃወም ለዓለም መንግስታት አስታውቀዋል። ከዚህ ጋር በተያያዘ የኢትዮጵያ ሙስሊሞችን በመከፋፈል አገሪቱን ወደ አስከፊ አዘቅት ውስጥ እየከተታት ይገኛል።የእምነት ተቋማቶች መሪዎች ህዝብ የመረጣቸው ሳይሆኑ መንግስት ለራሱ እንዲመቸው የመረጣቸው ሲሆኑ ህዝብን ሳይሆን ለታሪክ አተላ ለሆነው ለወያኔ የስራ አስፈፃሚ ካድሬ ከሆኑ ይኸው 21 ዓመት ሞላቸው።

በኢትዮጵያ የነፃ ፕሬስ ነፃነት ከመቼውም በላይ አስጊና አደገኛ ሁኔታ ላይ ይገኛል።በቅርቡ እንኳን አምባገነኑ የወያኔ መንግስት በእነእስክንድር ነጋ ላይ የ18 ዓመት እስራት ሲፈርድባቸው በተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች ላይ ከ15 ዓመት እስከ እድሜ ልክ ፈርዶባቸዋል።ይህንን ጉዳይ የአለም መንግስታት በፅኑ የተቃወሙት ሲሆን አሁንም ያሉት የተቃዋሚ

ፓርቲ መሪዎችና ጋዜጠኞች ወከባና እንግልት እየደረሰባቸው ይገኛሉ።

በአሁኑ ሰዓት አስከፊውን የወያኔ መንግስት በመጥላትና በመሸሽ አገራቸውን ጥለው ለስደት የሚዳረጉ ዜጎች ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ ሄዷል።እንዲሁም በመንገድ ላይ አውሬ የበላቸውና በባህር ሰጥመው መንገድ ላይ የቀሩ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ስፍር ቁጥር የላቸውም።

ባለፈው ዓመት በቱኒዝያ የተነሳው የህዝብ አመፅ በብዙ አገራት ግቡን የመታ ሲሆን በዴሞክራሲ እጦት ታፍነው የኖሩ ህዝቦች በአሁኑ ሰዓት በሰላምና በዴሞክራሲ ይኖራሉ።እኛም ከቱኒዝያ አብዮት በመማር ጨካኙንና አረመኔውን የወያኔ መንግስት በተቀጣና በገነፈለ የህዝብ አመፅ እንደሚያንኮታኩተው አንዳችም ጥርጥር የለንም።ድል ለሰፊው ህዝብ!

# በጋራ እንታገል

Milky Wolde/ löhne

ኢትዮጵያን ማየት የብዙ ኢትዮጵያዊያን ፍላጐት ነው ብዬ አምናለሁ የዜጐች ነጻነት የተከበረባት የህግ የበላይነት የነገሰባት እኩልነት የሰፈነባት ዲሞክራሲ የነገሰባት ኢትዮጵያን ማየት የብዙ ኢትዮጵያዊያን ፍላጐት ነው ብዬ አምናለሁ፡፡

ግን አሁን ያለው ዘረኛ መንግስት የናፈቅናትን ዲሞክራሲ የሰፈነባትን ኢትዮጵያን እንዳናያት አድርጐናል፡፡ ወያኔ በትረ ስልጣን ከያዘ ጊዜ ጀምሮ በመላው ሃገሪቱ የተረጋጋ ሰላም ጠፍቷል፡፡ ወያኔ የኢትዮጵያን ሕዝብ ሲያሻው በዘር፣ ሲያሻው በጐሳ፣ ሲያሻው ደግሞ በሃይማኖት ከፋፍሎታል ለዘመናት ተዋዶና ተከባብሮ አልፎም ተርፎ ተዋልዶ የኖረውን የሙስሊም እና የክርስቲያንን እምነት ተከታዬች እርስ በእርሳቸው እንዳይስማሙ ክብሪት ሲጭር ይታያል፡፡ ወያኔ አሁንም ለከፋት ስህተት ታጥቆ ተነስቶአል በተሳሉ ስለቶች በነፈዙ ጭንቅላቶች ዛሬም ኢትዮጵያ በቁጥጥር ስር ነች እያለ ይፎክራል፡፡ አሁን እኔ የወያኔ መንግስት እያደረገ ስላለው ነገር ልተርክ አልወድም ምክንያቱም ሃገር ያወቀው ጸሃይ የሞቀው የአደባባይ ሚስጥር ነውና። ስለዚህ መናገር የምፈልገው ማድረግ ስላለብን ነገር ነው አለበለዚያ ምንም ማድረግ ካልቻልን ወያኔ ሲያጠፋ እኛ ደግሞ ጥፋቱን ስናወራ ልንኖር ነው ስለዚህ ይሄ ጨካኝ መንግስት በስልጣን ላይ እንዳይቆይ ምን ማድረግ አለብን?

ለኔ እንደሚሰማኝ ከሆነ አንዱና ብቸኛው አማራጭ ሕዝብን ማእከል ያደረገ ሰፊ ትግል ነው፡፡ በዲሞክራሲና በነጻነት ስም በኢትዮጵያና ዜጐችዋ ላይ የተጫነውን የአገዛዝ ቀንበር መስበር አለብን፡፡ የሚል ጽኑ እምነት አለኝ ኢትዮጵያ ለእልፍ ልጆችዋ ገሃነም ለጥቂት ገዥዎች ደግሞ ገነት ከሆነች ዘመናት ተቆጥረዋል ስለዚህ ሁላችንም ለሃገራችን ማድረግ ያለብንን ለማድረግ “ቆርጠን መነሳት“ አለብን አለበለዚያ የዚያች የምንወዳት ሃገራችን መጨረሻዋ የከፋ ነው የሚሆነው፡፡ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር

# የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በቅርቡ ወደ መቃብር ይወርዳል

Yohanes Samson /Bad Hersfeld

የመለስ ዜናዊ የዘረኝነትና የአምባገነንነት አገዛዝ ከእንግዲህ ተቀብሮ ታሪክ ይሆናል እንጂ አይቀጥልም ታሪክም እንደሚያስረዳው አሁንም እንደምናየው የአምባገነኖቹ ለህዝባቸው እንደሚያወርሱት ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚሻገረው ቀጣይና ያማረ ታሪክ የላቸውም መልካሙንም ሞት አይሞቱም፣ የሞትንም ሞት ይሞታሉ፡፡ የሚያመልኩት ታንካቸውና ጦራቸው አስከፊውን የሞት ጽዋ ከመጠጣት አያድናቸውም በመለስ ዜናዊ የሚዘወረውን የወያኔ ጐጠኛ ቡድንም ከጐጠኛ መሪዎቹ ጋር ለህግ የሚቀርብበት ጊዜ ቅርብ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ከእንግዲህ በጐጠኝነት የተሰባሰበውን የወያኔ ቡድን የሚሸከም ትከሻ የለውም ከነ ታሪካቸው ወደ መቃብር ያወርዳቸዋል እንጂ።አሁን ባለንበት የ21ኛው ክፍለ ዘመን የአለም ህዝቦች አለምንም አንድ መንደር አድርጐ አብሮ የመኖር ለውጥ ሲኖር የኛዎቹ የዘመናችን የወያኔ ባዕድ መሪዎች መለስ ዜናዊና ተከታዩቹ ኢትዮጵያዊና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት የዘረኝነትና የጐጠኝነት ቀንበር በስውር አንግበው በህገ-አራዊት ህግ ለአንድነት ጥሩ የሆነውን የኢትዮጵያን ህዝብ እስር ቤት በማጐር በማሰቃየትና በማጐር በመግደል እጃቸውን በንፁሃን ዜጐች ደም የታጠቡ አምባገነኖች በመርዘኛ ምላሳቸው የአለሙን ህብረተሰብ በማታለል ኢትዮጵያን የመበታተን ስውር አጀዳቸውን በብብታቸው ስር ደብቀው 20 አመት ያልተሳካ ኢትዮጵያን የማጥፋት ቀመር በመስራት ላይ ይገኛሉ፡፡ ከእንግዲህ የወያኔ ዘረኛ መሪዎችን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የኢትዮጵያ ህዝብ በአንድነት የህዝባዊ አመጽ በማድረግ ከዘረኝነት ቀንበራቸው ጋር በቅርብ ጊዜ ወደ መቃብር ያወርዳቸዋል፡፡

# የወያኔ የኢንተርኔት ላይ ዘመቻ

Samuel Menase /Münnerstadt

በዓረቡ አለም የተከሰተው የሕዝብ አመጽ ቴክኖሎጂ ለነጻነት፣ ለዲሞክራሲና ለህዝቦች ሉዓላዊነት ያደረገውን አስተዋጽኦ በግልጽ አሳይቷል፡፡ በተለይ በጨቋኝ አገዛዝ ሲማቀቁ የነበሩት የዓረቡ ዓለም ህዝቦች ቴክኖሎጂን በመጠቀም መረጃዎችን በመለዋወጥ በአምባገነን ስርዓቶች ላይ ተጽእኖ ማድረግ ችለዋል፡፡ ቀደም ብሎም ቢሆን ቴክኖሎጂ የሚያመጣውን የህዝቦች ሉዓላዊነት ከወዲሁ በመፍራት ቻይና እና ኢራን የኢንተርኔት ዝውውሮች ላይ ጠንካራ እርምጃዎችን ሲወስዱ ቆይተዋል፡፡ የኢትዮጵያ አምባገነን መሪዎችም የቻይናና የኢራን የቴክኖሎጂ አፈና ስርዓቶችን ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡ በኢትዮጵያ የኢንተርኔት ሳንሱር በከፍተኛ ሁኔታ ተግባራዊ እየተደረገ ቢሆንም ህዝቡ ግን ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ኢንተርኔትን በመጠቀም የፖለቲካ አስተያየቶችን መለዋወጥ ጀምሯል፡፡ ነገር ግን የትግል ስልቱ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ የሚጠብቀውን አስተዋጽኦ እንዳያበረክት የሚጋርዱ በርካታ ፖለቲካዊ እርምጃዎች እየተወሰዱ ናቸው፡፡ አንደኛው አነስተኛ የተባለው የኢንተርኔት ሽፋን ሲሆን ሌላኛው ደግሞ የኢንተርኔት ሳንሱር ነው፡፡ መረጃዎች እንደሚያመላክቱት የኢትዮጵያ የኢንተርኔት ተደራሽነት ከአጠቃላይ ህዝቡ 1 በመቶ እንኳን አይሞላም፡፡ የኢንተርኔት ሳንሱርም

ቢሆን ሃገሪቱ ከቻይና መንግስት በሚደረግለት ድጋፍ የኢንተርኔት ሳንሱሩን (Deep packet Inspection (DPI) በተባለ መሳሪያ አጠናክራ ቀጥላበታለች፡፡ Sampsonia way በተባለ ድረገፅ ላይ የተለያዩ ጽሁፎችን የሚያቀርበው የመስፍን ነጋሽ ዘገባ እንደሚያመለክተው በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ከ150 በላይ ዌብሳይቶች፣ ብሎጐችና የፌስቡክ ገጾች ተዘግተዋል በኢንተርኔት የሚሰራጩ ጋዜጦችም በከፍተኛ ሁኔታ ሳንሱር እየተደረጉ ናቸው፡፡

አሁን ደግሞ በቅርቡ ኢንተርኔትን በመጠቀም የሚደረግ የድምጽ ጥሪ (Voice –over Internet –Protocol) Skype እና Google talk ጨምሮ ማንኛውም የድምጽ ጥሪ በአዋጅ ተከልክሏል፡፡ ህጉን ጥሶ የተገኘ ግለሰብ እስከ 15 ዓመት በሚዘልቅ እስራትና በከፍተኛ የገንዘብ መቀጫ እንደሚቀጣ ነው የተገለጸው፡፡

# የጨለማው ቀን

**Wube Alemayehu /Münnerstadt**

በሽብርተኝነት ክስ የፍርድ ሂደታቸውን ሲከታተሉ የነበሩት ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ እና ሌሎች 23 ግለሰቦች ባለፈው ሰኔ 27 የጥፋተኝነት ውሳኔ ተላልፎባቸዋል፡፡ ተከሳሾቹ የጥፋተኝነት ውሳኔ ሲተላለፍባቸው በፍርድ ቤት የተገኙት ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ እና ሌሎች 7 ግለሰቦች ብቻ ነበሩ፡፡ ቀሪዎቹ 16ቱ ግለሰቦች በተለያዩ ሃገራት በስደት ባሉበት ነው ውሳኔው የተላለፈባቸው፡፡ ከእነኚህ ውስጥ አምስቱ ጋዜጠኞቹ ናቸው፡፡ ተከሳሾች የጥፋተኝነት ውሳኔ የተላለፈባቸው የአምባገነኑ የመለስ ዜናዊ አስተዳደር በሽብርተኝነት ከፈረጃቸው ከግንቦት 7 እና ከሌሎች ድርጅቶች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል ለመቀየር ተንቀሳቅሰዋል በሚል ነው፡፡ ተከሳሾቹ ህዝብን ለአመጽ ተግባር በማነሳሳት፣ በሃገር ክህደትና በሌሎች ክሶችም ወንጀለኛ ተብለዋል፡፡ ውሳኔውን ያስተላለፈው ዳኛው ተከሳሾች በኢትዮጵያ ልክ እንደ ዓረቡ አለም አመጽ በማስነሳት ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በሀይል ሊቀይሩ ሲንቀሳቀሱ ነበር ብሏል፡፡

ይሁንና የሰብአዊ መብት ተቆርቋሪ ድርጅቶች እንደገለጹት በእለቱ የቀረቡት የፍርድ ቤት ማስረጃዎች ግለሰቦቹ የወንጀል ድርጊት እንደፈጸሙ ሳይሆን ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብታቸውን በመጠቀም በሰላማዊና ህጋዊ መንገድ ትግል ማድረጋቸው ነው፡፡ የኢትዮጵያ መንግስት በብሄራዊ ደህንነት ስም በአስተዳደሩ ላይ የሚሰነዝሩ ጋዜጠኞችንና ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ለማፈን ያደረገውን ሴራ በግልጽ ያሰየ ነው ሲሉም የፍርድ ሂደቱን አውግዘውታል፡፡ የፍርድ ሂደቱን በርካቶች በህግ የበላይነት ላይ የተደረገ "ስላቅ " ሲሉት አምነስቲ ኢንተርናሽናል ደግሞ "የጨለማ ቀን" ሲል ገልጻታል፡፡ ሂዩማን ራይትስዎች ውሳኔው የኢትዮጵያ መንግስት ቀላል የሚባሉ ትችቶችን እንኳን ለመታገስ ፍላጐት እንደሌለው ያሳያል ብሏል፡፡

# ወያኔና የኢትዮጵያን ታሪክ የማጥፋት እቅዱ

**Selam Fekre/Bayreuth**

የኢትዮጵያ ሕዝብ በወያኔ አገዛዝ ስር ከወደቀ ወዲህ ከፍተኛ ችግር ላይ ወድቋል፡፡ እንደሚታወቀው ወያኔ ሥልጣን ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ ሲገድል ሲያሥር ሲገርፍ ሲያሣድድና የሡብዓዊ መብትን ሲነፍግ ዛሬ ላይ ደርሷል፡፡

ይህን ጨቋኝ መንግስት ለመጣል የሚደረገው ትግል በአሁኑ ጊዜ በሁሉም የዓለም ህዝቦች ውስጥ ቦታ እንዳያገኝ እያደረገ ያለው ሙከራ አንዱ ነው፡፡ ይኸውም የአፍሪካ ሕብረት ህንጻ በአዲስ አበባ ተሠርቶ በተመረቀበት እለት በህንጻው ፊት ለፊት መሪዎች መካከል አጼ ሃ/ስላሴ አንዱና ዋንኛው እንደነበሩ ሁሉም የሚያውቁው እውነት ነው ለወያኔ መንግስት ግን እኒህን የመሠሉ ታሪኮች አይዋጡለትም፡፡

ወያኔ ታሪክ የማጥፋቱን ሥራ በመቀጠል የአጼ ሃ/ስላሴን ሃውልት ቢያቆም ጥሩ የታሪክ አጋጣሚ ነበር፡፡ ነገር ግን የኢትዮጵያን ታሪክ ለማጥፋት የሚንቀሳቀስ ስለሆነ የክዋሜ ንኩርማህን ሃውልት በማቆም የኢትዮጵያን ታሪክ የማጥፋቱን ሥራ ተያይዞታል፡፡

ታሪክ ለሁልጊዜም እኚሁን ታላቅ የኢትዮጵያን መሪ ያሥታውሣቸዋል፡፡ ይሁንና ወያኔ በእያንዳንዱ ታሪካችን ላይ ትልቅ ጠባሣ ጥሎ ለማለፍ የሚያደርገውን እንቅስቃሴ እና የኢትዮጵያ ውድ ልጆች በአንድነትና በህብረት ታሪካችንን የማሥጠበቅ ሃላፊነት ስላለብን ከዛሬዋ ቀን ጀምሮ በአንድነት እንነሣ እላለሁ፡፡እግዚአብሄር አምላካችን ኢትዮጵያን ይባርክ!ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር

# ሁሉም ይንቃ

**Fekerte Gebre /Aschaffenburg**

ኢ-ዲሞክራሲያዊው ወያኔ ስልጣኑን ለማራዘም ከሚጠቀምበት ዘዴዎች ውስጥ ሃይል አንዱ ሲሆን ሌላው ደግሞ ህዝቡን በተለያየ መንገድ በመከፋፈል እርስ በርሱ እንዳይግባባ እና እንዳይተማመን በዘር፤ በሃይማኖት በመከፋፈል ማጋጨት ትልቁ ፕሮግራሙ ነው፡፡

ጸረ ህዝቡ ወያኔ በቅርቡ እያደረገ ያለው ሌላኛውን ህዝብን የመከፋፈያ ዘዴ ደግሞ በተለያዩ አገሮች የሚገኙ ኢትዮጵያውን /ዲያስፖራ/ በጥቅም መሸንገል ሆኗል፡፡

ከኢሕአዴግ ጋር የተስማማውን ሃገር ቤት የቤት መስሪያ ቦታ በመስጠት እና ከቀረጥ ነጻ ዕቃ በማስገባት መገፋፋትና በይስሙላ ጥቅማ ጥቅም

በማቁለጭለጭ በውጪ ሃገር የሚደረግበትን ጫና ለመቀነስ እየተራወጠ ነው፡፡

የሃገራችንን ምስኪን ጥሩ በልቶና ጥሩ ለብሶ እንዲያድር ማድረግ ያልቻለ መንግስት ከኔ ጋር ካበራቹ ይህንን ጥቅማ ጥቅም ታገኛላቹ እያለ በውጭ ሃገር ላሉ ኢትዮጵያውያን የሚደሰኩረው አሰበልን ሳይሆን በዙር ጥምጥም የራሱን የስልጣን እድሜውን ለማራዘም እንደሆነ ሁላችንም ተረድተን በአንባገነኑ ወያኔ ላይ የምናደርገውን ተቃውሞ ሁላችንም በመተባበር እንቀጥል፡፡

# እሱን ብሎ መሪ

Sami Solomon /Schweinfurt

የኢትዮጵያ ሕዝብ በዚህ ወቅት ለሚመጡ የመለስ ዜናዊ ማስፈራሪያዎችና ማዘናጊየዎች ጆሮዎቹን መድፈን አለበት ፡፡

መለስ ዜናዊ ከሥልጣን እስካልተወገደ ድረስ የኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞችም ሆኑ ክርስቲያኖች አንዳችም መብት፤ አንዳችም ነጻነት እንደማይኖራቸው ማመን ይገባል ይህ እምነት ደግሞ እያደር በሁሉም ወገኖች ሰፊ ተቀባይነት እያገኘ ነው፡፡

ሙስሊምም ሆነ ክርስቲያን የሆንን ኢትዮጵያውያን በሙሉ መለስ ዜናዊ ቁርጥህን እወቅ፤ እኛ አንለያይም!!! እንድንለው ያስፈልጋል፡፡ ዛሬ በአገራችን ታሪክን የሚያጣፋ ፤ ማንነታችንን የሚያዋርድ ኢትዮጵያዊያንንም የማያውቅ፤ ሰማይንና ምድርን የሰራን እግዚአብሄርን የማይፈራ የውስጥ ጠላት ተነስቷል መለስ ዜናዊ አምባገነን ነው፡፡ መለስ ዜናዊ አምባገነን ነው!! ነጻነትን እንፈልጋለን መለስ በስብእና ላይ ወንጀል የፈጸመ ነው መለስ ወንጀለኛ ነው!!! ፣ ምግብ ያለ ነጻነት ምንም ማለት አይደለም የፖለቲካ እስረኞች ይለቀቁ ነጻነት እንሻለን መለስ አምባገነን ነው ነጻነት!! ነጻነት!! ነጻነት!! ለሰፊው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ይሁን ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!

# ጸረ ትውልድ

Alem Tesfa Asfaw /Bayreuth

በአገራችን ኢትዮጵያ 85% ህዝብ በግብርና ሙያ ይተዳደራል አገራችን ከፍተኛ የተማረ የሰው ሃይል እጥረት ከአለባቸው አገሮች አንዷ ናት፡፡ እንደሚታወቀው ሁሉ የተማረ የሰው ሃይል ቀጣይነት ላለው ኢኮኖሚ ግንባታ ወሳኝ ነው፡፡ የወያኔ መንግስት ባለፉት 20 ዓመታት የተማረ የሰው ሃይል ቁጥር በመጨመር ኢኮኖሚ አሳድጋለሁ ብሎ የሚታየው ጥራት በሌለው የት/ት ፖሊሲው ያሰለጠናቸውን ምሩቃን ከሞያቸው ውጭ ማንኛውም ተራ ያልተማረ ሰው ሊሰራ የሚችላቸውን ሥራዎች በማሰራት ላይ ይገኛል፤ ከዚህም መካከል ዋናው ተጠቃሽ ሊሆን የሚችለው በአሁኑ ወቅት በድንጋይ ጠረባ /ኮብልስቶን/ ሥራ ላይ የተሰማሩ የመጀመሪያና የሁለተኛ ዲግሪ ያላቸው ምሩቃን በብዛት መገኘታቸው ነው፡፡

ዜጐች ሥራን ሳይንቁ መሥራት ለራሳቸውም ሆነ ለአገራቸው ጠቀሜታ ቢኖረውም 85% ያልተማረ ህዝብ በሚኖርባት ኢትዮጵያ ግን የተማረው ህዝብ በእንደዚህ አይነት ሥራ ላይ ለመሳተፍ መገደዱ የአገሪቱን የልማትና የእድገት ፖሊሲ አቅጣጫ ውጤታማነት ጥያቄ ውስጥ የሚከት ነው፡፡ ይህም ሁኔታ የሚያመለክተው የወያኔን መንግስት ሥራ መፍጠር አለመቻልና ከአገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ ጋር የማይመጣጠን የት/ት ፖሊሲ መከተሉ ነው፡፡

ስለዚህ እብሪተኛውን የወያኔ መንግስት ከማንኛውም የትግል አማራጮች ለማስወገድ ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ ሊነሳ ይገባል፡፡እግዚአብሄር ኢትዮጵያን ይባርክ!

# የወያኔ ተንኮልና መዘዝ

Marta Eyob Seyum /Homberg (Efze)

ኢትዮጵያ አፍሪካና መካከለኛውን ምስራቅ በመሰንጠቅ አለማቀፍ አቋራጭ የንግድ መተላለፊያ የነበራት የቀይ ባህር ባለቤት ነበረች፡፡ ወያኔ ስልጣኑን ሲፈናጠጥ የመጀመሪያው ተግባሩ የባህር ወዳብ ባለቤትነቷን ማሣጣት ነበር፡፡ ከዚህም ባለፈ በቋንቋና በዘር የተመሰረተ የክልል ማካለል በማድረግ አንድ አይነት ባህል የነበረውን ህብረተሰብ ክፍል በመከፋፈልና በማጋጨት ላይ ይገኛል።ወያኔ የተቃዋሚ ፖለቲካ ሃይሎችን በነፍጥና በእስራት በመደፍጠጥ አንዳንዶችንም በሃገር ውስጥ እንዳይንቀሣቀሱ በማገድ በብዙሃኑ ሥም የአንድ ፓርቲ ሥርዓት የነገሰባት አድርጐ በመስራት ገበሬው በእርሻ መሬት እጦት ቀየውን ለቆ እንዲወጣ ነገር ግን በሚሊዬን ጋሻዎች የሚቆጠር ለም መሬት የውጭ ኩባንያዎችና ከበርቴዎች የሚቸበቸቡበት፣ ውሃ ገብ የሆኑ በሃገራችን ምእራባዊ ወሰን የሚገኙ ለም መሬቶችን በመቸብቸብ፤ ይህም ሣያንሰው በዘር የቋንቋ የባህል ትስስሩ ጠንካራ በሆነ ህዝብ ውስጥ ጥርጣሬና ጥላቻን አራግቧል፡፡

በዚህም በምሣሌነት ልንጠቅሰው የምንችለው በደቡብ ኢትዮጵያ ይኖሩ የነበሩ የአማራ ተወላጆች አማርኛ በመናገራቸው ብቻ ህጻናት ከትምህርት ገበታቸው ላይ በማሥነሣት እናቶችና አባቶች ቤትና ንብረታቸውን ብሎም እርሻቸውን ጥለው እንዲሄዱ ተገደዋል፡፡ በዚህም መሰረት በሃገራቸው ላይ ተንከራታች እንዲሆኑ ተገደዋል፡፡ ስለሆነም በትውልድ መካከል የማይሽር ጠባሳ ጥለው ለማለፍ ከመጀመሪያው የተነሱበትን የእባብ መርዛቸውን በመርጨት ላይ ይገኛሉ፡፡ በኢትዮጵያ

ውስጥ ዛሬ ህኑ የሚሰራው ለተቃዋሚና ለጭቁኑ ህዝብ በመሆኑ የሚገርምና የሚያስደንቅ ከመሆኑም በላይ ቁጣንም የሚቀሰቅስ ነው፡፡ በአንፃሩ ወያኔ ለህኑ ያልመገዛቱ በኢትዮጵያ ውስጥ የህግ የበላይነትና ነጻ የዳኝነት ሥርዓት እንዳይሰፍን ሆኗል፡፡

ወያኔ ኢትዮጵያ የምትባለውን ሃገር ለማጥፋት አጥብቆ የሰራ መሆኑ አጠራጣሪ አይደለም፡፡ በዚህም በሙቶ የሚቆጠሩ የጋምቤላ ተወላጆችን ሽፍቶች ናችሁ በማለት በጥይት እየተደበደቡና እየተፈናቀሉ ይገኛሉ፡፡ በዚህ መሰረት የወያኔ እቅድና አላማ ኢትዮጵያንና የኢትዩጵያን አንድነት ማጥፋት እስከ ሆነ ድረስ ሃገር ወዳድ የሆናችሁ በሙሉ ሃገራችንን የማዳን ሃላፊነት ስላለብን በአንድነት በመነሣት የወያኔ ስርዓት ከሥሩ ማስወገድ ይገባናል እላለሁ፡፡

# የሽብርተኝነት ሥያሜ በኢትዮጵያ

**Ribka Lemma Taye /Homberg (Efez)**

ህዝብን የሥልጣን ባለቤት ለማድረግ መታገል፣ ሃሣብን በነጻ መግለጽ፣ የዲሞክራሲ ተቋማት ግንባታ ማካሄድ ሃሣብንና ነጻነቱን እንዲገልጽ ማድረግ፣ ገለልተኛና ነጻ የሆነ የሰብአዊ መብት ተመልካች ተቋም ይቋቋም የሚል ንቁ ተሣትፎ ያለው ግለሰብ በወያኔ ትርጉም አሸባሪ ነው፡፡

ድንግል የኢትዮጵያን መሬትን ለአረቦች ለኢሲያ ቱጃሮች ሲሸጡ ይህ ለሃገር እድገት የሚያመጣው ፍይዳ የለም ብሎ ሃሣብን መግለጽ አሸባሪነት ነው፡፡ ሰላማዊ ሰልፍ እንውጣ ይፈቀድልን ብለው ለመንግስት ጥያቄ ያቀረቡ ያገሪቷ ብርቅዬ ታጋዬች አሸባሪ ተብለው ጠያቂ በተከለከለበት ቦታ ወደ ጨለማ ተጣሉ፡፡ ወደ አዘቅት ወረዱ፡፡ ከነዚህም ውስጥ ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ፣ አንዱአለም አራጌ፣ እና ወይዘሮ ርዮት አለሙ ለአብነት ይገኙበታል፡፡ ኢሕአዴግ ስልጣን ከያዘበት አንስቶ ከአሜሪካ አራት ፕሬዘዳንቶች ተቀባብለው፣ በእንግሊዝ 4 ጠቅላይ ሚኒስተሮች ተለዋውጠዋል፡፡ ቻይና እንኳ የኮሚኒስት ፓርቲ ሥልጣን አይልቀቅ እንጂ 3 መሪዎችን አይታለች፡፡

በኬንያ ነባሩ ካኑ ፓርቲ ለተቃዋሚዎች ሥልጣን አጋርቷል፡፡ ደቡብ አፍሪካ ሶስት መሪዎች ለዋውጣለች፡፡ በዛምቢያም 3 መሪዎች ሥልጣን ተረካክበዋል፡፡ ኢትዮጵያ ስሜን ከሪያና ኩባ የመሣሠሉት ጥቂት ሃገራት የአንድ ፓርቲ ሥልጣን ላይ ለረጅም ጊዜ መቆየቱ ያተረፈላቸው ሙስና፣ ኋላ ቀርነትና ድህነት ብቻ ነው። ኢትዮጵያ የበርካታ ታላላቅ ወንዞችና ጅረቶች ባለቤት ብትሆንም በእርሻ መሬት የምትጠቀምበት የመስኖ ውሃ ከሙቶ 1,6% ብቻ መሆኑን በዓለም ውስጥ እጅግ ድሀ ተብለው ከሚፈረጁት 12 ሃገሮች መካከል አንዷ ናት፡፡ ሥለሆነም በየትኛውም መስፈርት በአንባገነን መንግስት በትረ ሥልጣኑን ከያዘ ከ20 ዓመት በኋላ እድገት ያመጣል ብሎ ማሰብ ጨረቃ ዳቦ ጣይልኝ ሥለሚሆን ሁሉም የኢትዮጵያ ወጣት ሃይል በአንድነት በመነሣት ሥርዓቱን ማስወገድ ይጠብቅብናል እላለሁ፡፡

# የምንታገለው ሥርዐቱን ነው!!!

**Weldekiros Asfaw Abera/Bayreuth**

የወያኔ የኋላ ታሪክ እንደሚያሳየው ለረጅም አመታት በጋራ አመራር / Collective Leadership/ ይመራ የነበር ሲሆን በ1993 ዓ/ም የህወሃትን መሰንጠቅ ተከትሎ የሃገሪቱም ዕጣ ፈንታ ይሁን የወያኔ አመራር በመለስ ዜናዊ መዳፍ ስር መውደቅ ችሏል። ይህንንም ተከትሎ የወያኔ ካድሬዎችም ሆኑ የተለጣፊ ድርጅት የፖለቲካ አድር ባዮች /Opportunists/ ከሃገር አቀፍ ተቋማት ይልቅ ላለፉት አስራ አንድ አመታት የመለስን የፖለቲካ ተክለ-ስብዕና በመገንባት የተጠመዱት። ስለሆነም በስርዐቱ እና በመለስ መካከል ልዩነት ሳይኖር ላለፉት አስር አመታት መዝለቅ ችሏል።

ነገር ግን የመለስ በድንገት መታመምና ለወደፊትም ወደ ስራው የመመለስ ዕድሉ ጠባብ እንደሆነ እየተነገረ ባለበት ሁኔታ የወያኔ መስራች የሚባለው ስብሃት ነጋ መለስ ባይኖርም ሥርዐቱ እንደሚቀጥል ለ ቪኦኤ ከሰጠው መግለጫ መረዳት ይቻላል።በእርግጥ አቶ ስብሃት እንደተናገረው የወያኔ ሥርዐት ከግለሰብ አምልኮ /Cult of Individuals/ በአጭር ጊዜ ተላቆ የጭቆና ዘመኑን ለማራዘም እየጣረ ይገኛል።

በመሆኑም የኛ የትግል አቅጣጫ በአጠቃላይ በወያኔ ስርዐት ላይ ሊሆን ይገባል። ለዘመናት ዜጎቻችንን በማሰርና በማሰቃየት፣ዜጎቻችን ማህበራዊ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ፍትህ በማጣት እንዲሰቃዩ ብሎም በሃገራቸው ባዕድ ሆነው እንዲኖሩ ያደረገውን ስርዐት ሌላ ተጨማሪ የስቃይ አመታት ልንፈቅድለት አይገባም!!!


# የምንመራው በህግ ወይስ?

**Hiwot Tilahun /Zeil**

አምባገነኑ የወያኔ መንግስት ህገመንግስቱ ላይ ባስቀመጠው ህግ መሰረት ማንኛውም ሃይማኖት በራሱ ህግና ደንብ እንደሚተዳደርና መንግስት በእምነት ተቋማት ጣልቃ እንደማይገባ ይደነግጋል።ሆኖም እየተደረገና እየተሰራ ያለው ስራ አሳፋሪና አሳዛኝ ነው።

እ.ኤ.አ በ2004 ዓም በመጋቢት ወር ላይ የዝቋላ ገዳምን ሆን ብሎ በማቃጠልና ህዝቡ ቃጠሎውን እንዳያጠፋ በፌደራል ፖሊስና በመከላከያ ሰራዊት ዙሪያውን በማስጠበቅ ብዙ ታሪካዊ የሆኑ የቤተክርስቲያን ንብረቶች ተቃጥሏል።

ሌላው በጣም የሚያሳዝነው በተመሳሳይ ወቅትና ወራት የዋልድባ ገዳም እጅግ በጣም ብዙ የሆኑ ታሪካዊ የሃይማኖት መፅሃፍትና ታቦቶች


THE PEOPLE DON'T KNOW
THEIR TRUE POWER.

የሚገኙበትን ጥንታዊና ታሪካዊ ገዳም ለግል ባለሃብት በልማት ስም በመሸጥና የሃይማኖት አባቶችን ብዙ ጊዜ ከኖሩበት ቤተ እግዚአብሔር በግፍ በማሳደድና በማሰር ብሎም በመግደል እንዲሁም የአባቶችን ክብር በመናቅና ያላቸውን ክብር በማዋረድ አሳፋሪ ተግባሩን በማከናወን ላይ ይገኛል በመሆኑም ድር ቢያብር አንበሳ ያስር ነውና በህብረት የወያኔን መንግስት ለማስወገድ እንነሳ።

# የህዝቤ ነፃነት ናፈቀኝ

Foziya Chacho/Windsbach

አምባገነኑ ወያኔ በህዝቡ ላይ የሚያደርሰው ግፍና መከራ መቼ ነው የሚያበቃው? ለወያኔ ስለፍትህ፣ነፃነትና ሰላም ማሰቡም ሆነ ከቶ የማይታሰብ ነገር ነው።ምስኪኑ ህዝቤ ስለሙብቱና ነፃነቱ የሚናገርና የሚጠይቅ ካለ ዛቻ፣እስራት፣ግርፋትና መግደል ነው እጣ ፈንታው።ለአንባገነኑ ወያኔ ታዲያ ትልቅ ዲሞክራሲ ነው።

የነገውን አገር ተረካቢውን ትውልድ በመጨፍጨፍና በዘር በመከፋፈል ታሪካዊ ገዳማትን ለውጭ ባለሃብት በመሸጥና በማቃጠል ነፃ ፕሬስ የተከለከለበት ፖለቲከኞችና ጋዜጠኞች በግፍ የሚታሰሩበትና የሚሰቃዩበት በአንባገነኑ ወያኔ እጅ ላይ ነው ያለነው።ታዲያ ጎበዝ ዛሬ ፍትህና ነፃነት ለናፈቀው ህዝብ ቢጋራ የሚያስተባብረው ቢያገኝና በተባበረ ክንድ ቢነሳ አጅሬ ወያኔ ድምጥማጡ እንደሚጠፋ ጥርጥር የለኝም። "ኢንሻ አላህ" የተባበረ ክንድ ያሸንፋል።

# አደራው ለማን ነው

Tedi Awel Welde/Neuburg

ጠቅላይ ሚንስትር መለስ ዜናዊ ለ21 ዓመታት ሙሉ በግፍና ጭቆና የገዙትን የኢትዮጵያ ህዝብ አደራ የሚሉት ለማን ይሆን? ለቀዳማዊት እመቤት አዜብ መስፍን ወይስ ለፐሬዝዳንት ግርማ ወልደጊዮርጊስ?ኧረ ለማን ይሆን አደራው? የመለስ ዜናዊ አይናቸው ፈጦ አንገታቸው ተደፍቶ ሳይቀር በቁማቸው የቁም ኑዛዜ ቢናዘዙ አይሻላቸው ለዘመናት በንፁሃን ዜጎች ደም የተነከረ እጅ ወዴት ይሆን ጉዞው? ገሃነብ እሳትም ብትሆን የዚህን ሰው ነፍስ እንዴት ትቀበለዋለች? ምክንያቱም ሰውነቱ በሙሉ በንፁሃን ዜጎች ደም ተነክሯል።ምን ይሆን የመለስ መጨረሻ? ማንንስ ይቅርታ ይጠይቅ እግዚአብሔር አምላክን ወይስ ወዳጁን የቅርብ አማካሪውን ሰይጣንን? ጉድጓዱ ተቆፍሮ ተምሶ ወዳጁ ዲያብሎስ ና ወደ እኔ እያለው ነው። ምን ይሆን የመለስ መልሱ? መለስ አንዴ ቀና በል አይንህንም አታፍጥ አንገትህንም አትድፋ አይዞህ አትደንግጥ።የአበበ ገላው ቃል ሆነብህ የደም ካንሰር ወይስ የጭንቅላት እጢ? ነው ወይስ አቦዬ ገ/መንፈስ ቅዱስ ተቆጡህ? ያ ሁሉ የንፁሃን ያፈሰስከው ደም አሰከረህ? መልሱን ላንተ።

እንግዲህ መለስ ልትሸኝ በዝግጅት ላይ ነህ እንግዲህ በዘመንህ የሰራኸውን ስራ አስብ።ምን እንደሆነ የሰበሰብከውን የሃገራችን ንብረት የዘረፍከው የንፁሃን ዜጎች ላብ ገንዘብ በተለያዩ የውጭ ሃገር ባንኮች ያከማቸኸውን ገንዘብ ይዘኸው ልትሄድ አሰብክ? ወይስ ለልጅ ልጅህ ልታወርሰው? ይገፔው እሄዳለው ካልክ ሳጥንህን ሰፊ እና ጉድጓድህን አስፍተን እንድንቆፍርልህ እንግዲህ መልዬ በቁምህ በህይወት ሳለህ አሳምር ምርጫህን።

# መወገድ ያለበት ወያኔ

Mohamednur Sadat Anwar/ Regensburg

የወያኔ መንግስት ያለምንም ተቀናቃኝ በትረ ስልጣኑን የግል አድርጓል። በርግጥም ወያኔ በምርጫ ብዙ የንፁሃንን ደም ጭምር በማፍሰስ ለኢትዮጵያ ህዝብ በቂ ትምህርት ሰጥቶ በምርጫ ያላሸነፈው ወያኔ በሃይል መግዛቱን ቀጥሏል። በወያኔ መንግስት ግፍና ጫና የተነሳ ሃገር ትቶ የሚኮበልለውን ቤት ይቁጠረው። ወጣት ተምሮ ሃገር በመጥቀም ፈንታ የወያኔን ግፍአዊ አስተዳደር በመሸሽ በስደት ላይ እንገኛለን። ወያኔ አሁንም ግፍና ተንኮሉን አላቆመም። በቅርብ ስንት ኢትዮጵያውያን በበረሃ የውሃ ሽታ ሆነው ቀርተዋል። ወገን ዛሬውኑ በመነሳት ይህንን ወያኔ እናስወግድ።

# የኢትዮጵያ ህዝብ በወያኔ መንግስት ተጨቁኗል

Biruk Hailu/Regensburg

የወያኔ መንግስት ያለምንም ተቀናቃኝ የስልጣን በትሩን በህዝብ ላይ ማድረጉን አሁንም አላቆመም።ወያኔ በህዝብ ላይ እያደረገ ያለው ኢሰብአዊ ግፍና እንግልት አልበቃም ብሎት በቅርብ ደግሞ ህዝብ በሰላም ተከባብሮ የኖረባት በሃይማኖት ተቻችለው የኖሩባት ይህች ሃገር ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ በወያኔዎች ጠንሳሽነት አንዱን ከአንዱ በማጋጨት የተንኮል ስራውን መስራቱን ቀጥሏል። እኛም ይህንን የወያኔን ተግባር ተንኮሉን በመረዳት በአንድ ላይ በህብረት በመሆን ይህንን አሳፋሪ ተግባር በህብረት በመሆን ማስወገድ አለብን!

# አሸባሪው ማነው?

Daniel Fanta/Münnerstadt

ከሶስት ዓመት በፊት የፀደቀውን የኢትዮጵያ የፀረ ሽብርተኝነት አዋጅ ተከትሎ በርካታ ጋዜጠኞች፣ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎችና የሰብአዊ መብት ተቆርቋሪ አራማጆች በመታሰርና ከሃገር በመሰደድ ላይ ይገኛሉ። ባለፈው ጥር ወር ሶስት ጋዜጠኞች ከፀረ ሽብር አዋጁ ጋር በተያያዘ ወንጀለኛ ተብለው ተፈርዶባቸዋል። ሁለት የስዊድን ጋዜጠኞችም ከኦጋዴን ብሔራዊ ነፃነት ግንባር (ኦብነግ) ጋር ግንኙነት አላችሁ በሚል በፀረ ሽብር አዋጁ ወንጀለኛ ተደርገው እያንዳንዳቸው የ11 ዓመት ፅኑ እስራት ተፈርዶባቸው በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ በእስር በመሰቃየት ላይ ይገኛሉ።ከዚሁ ከፀረ ሽብር አዋጁ ጋር በተያያዘ ከ100 የሚበልጡ የኦሮሞ ብሔር

ተወላጆች ከኦነግና ከኦብነግ ጋር ግንኙነት አላችሁ በሚል በአሁኑ ወቅት በእስር ቤት ሆነው የፍርድ ሂደታቸውን በመከታተል ላይ ይገኛሉ። ባለፈው ሰኔ 27 ደግሞ 24 ግለሰቦች ከፀረ ሽብር አዋጁ ጋር በተያያዘ ወንጀለኛ ናቸው በሚል የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ አስተላልፎባቸዋል። ከእነኚህ ግለሰቦች ውስጥ ስድስቱ ጋዜጠኞች ሲሆኑ ቀሪዎቹ ደግሞ የተቃዋሚ ፓርቲ ከፍተኛ አመራሮችና የሰብአዊ መብት ተቆርቋሪ ግለሰቦች ናቸው። ባጠቃላይ ይህ ሁሉ የሚያሳየው የኢትዮጵያ መንግስት የፀረ ሽብር አዋጁን እንደሽፋን በመጠቀም በአስተዳደሩ ላይ ትችት የሚሰነዝሩ ጋዜጠኞችንና የፖለቲካ ፓርቲዎችን ለማፈን ያደረገው የፖለቲካ ሴራ እንደሆነ ነው። እናም አሸባሪው መንግስት ህዝብን ከማሸበር ተግባሩ እንዲቆጠብ እንጠይቃለን።

# ፍፃሜው የሚያስደነግጥ የአምባገነኖች ሩጫ

Eden Dawit/Gieβen

በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ሃገራችን እየተካሄደ ያለው ህዝቡን የማተራመስ እቅድ ሩጫው ወደየት እንደሚያመራ የማይታወቅ ሆኗል።በየትኛውም አቅጣጫ የኢህአዴግ አምባገነኖች የሚጠቀሙት መንገድ ህዝቡን እርስ በርስ ከማጋጨት ያለፈ አላማ አይኖረውም። የኢህአዴግ ጨፍጫፊና አምባገነን አመራር በህዝቡ ላይ የስነልቦና አለመረጋጋት እንዲኖርና ስለሃገሩ ሁኔታ በተለያየ መልኩ ኢንፎርሜሽን እንዲያገኝ የስካይፒ አገልግሎትን በማቋረጥ እና የተለያዩ የህትመት ድርጅቶችን ከገበያ በማስወጣት አስከፊ በደልና ጫና በማድረግ ላይ ይገኛል። በሌላም መንገድ ህዝቡ በሃገሩ እምነትና ልማድን በስርዐት ለማስፈፀም ከማይችልበት ደረጃ ላይ ተደርሷል።በቅርብ በሙስሊም ዜጎቻችን ላይ እየደረሰ ያለው በሰላም የፆም ጊዜያቸውን ለማሳለፍ ወደ መስጊድ በመሄድ ላይ ባሉትና በአካባቢው በተገኙት ሰዎች ላይ የድብደባና የግድያ ወንጀል ተፈፅሞባቸዋል። ይህ በሃገራችን እየታየ ያለው ያለመረጋጋት ምክንያት የኢህአዴግ አምባገነን መንግስት የሚከተለው ብልሹ ስልትና የሰላም ፀር እና ጦርነትና ረብሻ ናፋቂ አመራሮቹ ምክንያት መሆኑ ይታወቃል። ታዲያ ያገሬ ልጆች በአንድ ላይ ሆነን የዚህን አምባገነን መንግስት በደል ልናጋልጥ የምንችልበት ጊዜ አሁን ነው። በትግላችን ሃገራችንን ከአምባገነኖች ነፃ እናውጣት።ለዚህም ትግላችን ኢህአፓ ከጎናችን ይገኛል።እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ።

# አፈና በዛ

Zewdinesh Nigatu/Alsfeld

ዛሬ በሃገራችን ዜጎች ሃሳባቸውን በነፃነት እንዳይገልፁ ወያኔ አፋኝ የሆኑ የፕሬስ ህጎችን በማውጣትና ተግባራዊ በማድረግ ቅድመ ህትመት ሳንሱር / Censorship/ የጀመረ ሲሆን በቅርቡ ሳምንታዊ የሆነችውን የነፃው ፕሬስ ጋዜጣ ፍትህ ጋዜጣንም ዘግቷል።በኢትዮጵያ ውስጥ የኢንተርኔት ድምፅ ፕሮቶኮል / Internet Sound Protocol/ አገልግሎት ላይ እንዳይውል በማድረግ ይህንንም በሚተላለፉ ሰዎች ላይ እስከ 15 ዓመት በሚደርስ እስራት እንደሚቀጣ አስታውቋል።ሌላው የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎችና ጋዜጠኞችን በሽብርተኝነት ስም እየከሰሰ ለእስር፣ለስቃይና ለእንግልት ከመዳረጉም በላይ የፖለቲካ እስረኞች በእስር ቤት ውስጥ ከፍተኛ ድብደባ እየደረሰባቸው ይገኛል።ለምሳሌ በአቶ አንዷለም አራጌ ላይ የደረሰው ድብደባ፣በጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ በጨለማ ክፍል ውስጥ እንዲታሰር መደረጉ አሳዛኝ ነው። የሃገራችን ህዝብ በርካታ ችግሮች አሉበት።ወያኔ አረጋግጫለሁ የሚለው ዕድገት ከፍተኛውን ባለሃብት የጠቀመ ዝቅተኛውን ደሃ በልቶ ማደር የማይችልበት ሁኔታ የፈጠረ ሲሆን በየጊዜው የሚደርስበትን በደል መግለፅ ወደማይችልበት በአፈና ሥርዐት ውስጥ የሚማቅቅ ህዝባችንን ልንታደገው ይገባል።ለዚህም የተቃውሞ ድምፁን የሚያሰማበት ምንም ከፍተት የለም።በህይወት የመኖር መብቱ አደጋ ላይ ለወደቀው ህዝባችን የወያኔ የጭካኔ በትርና ተንኮል ከአቅሙ በላይ ሆኖበት አንገቱን የደፋውን ህዝባችንን ልንደርስለት ይገባል።ይህን አፋኝ ስርዐት በተቀናጀና በተደራጀ መንገድ ከስር ከመሰረቱ በመንቀል ህዝባችንን ነፃ ልናወጣው ይገባል።

# እጅ ለእጅ ተያይዘን ወያኔን ከጭንቅላታችን እናውርድ!

Meriam Kuraw/Windsbach

ከ1983ዓም ጀምሮ ለነፃነታችሁ ታገልኩላችሁ በማለት በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የሚቀልደው የወያኔ ድብቅ ሴራ ተደብቆ የማይቀር ነው።የኢትዮጵያ ህዝብ ከ3000 አመት በላይ በዘር በሃይማኖት ሳይከፋፈል አንድነቱን ጠብቆ መቆየቱ ለማንም የኢትዮጵያ ህዝብ የተደበቀ ታሪክ አለመሆኑን ታሪክ ይዘክረናል፡፡ነገር ግን የወያኔ መንግስት የኢትዮጵያን ታሪክ ወደጎን በመተው የራሱን የስልጣን ጊዜ ለማራዘም ከምርጫ 97 ጀምሮ ከጥንት አባቶቻችን ለትውልድ ጥለው ያለፉትን ታሪክ ወደጎን በመጣል በዘር፣በሃይማኖትና በጎሳ በመከፋፈል የራሱን አንባገነንነቱንና ዘረኝነቱን በገሃድ አውጥቶታል። ይህም ደግሞ የራሱን ስልጣን ለማቆየት ከ9 ዓመት ህፃን ልጅ እስከ አረጋውያን ድረስ በራሱ ታማኝ ወታደሮች ተገድለዋል። ሴት እህቶቻችንም በየጨለማው ተደፍረዋል። የንፁሃን ኢትዮጵያውያንን ደምም አፍስሷል።ይህ ደግሞ ዘመን የፈጠረበት ሳይሆን ወያኔ የራሱን አምባገነንነት ያንፀባረቀበትና የስልጣን ጊዜውን ማራዘሚያ ያደረገበት የታሪክ ጠባሳ ነው። ይህ ደግሞ ለማንም ኢትዮጵያዊ ከህሊናው የማይጠፋ ቁስል ብቻ ሳይሆን መርዘኛ ጭስ መሆኑ ህሊና ያለው ልብ ይላል።

ዛሬ ለኢትዮጵያ ህዝብ ነፃነት እኩልነት የሃይማኖትና የጎሳ ልዩነት ሳይኖር ተቻችሎ በመኖር በዲሞክራሲ መንገድ ለሃገር ክብር ሲባልና የህዝባችንን መብት

ለማስከበር ከደም መስዋዕትነት እስከ ህልፈተ ህይወት መስዋት በመክፈል የዜግነት ግዴታቸውን በመወጣት ግንባር ቀደም ሆነው የወያኔን ታሪክ አዳፋ ለማፅዳት ደፋ ቀና በማለት ቁርጠኝነታቸውን በማሳየት ላይ ይገኛሉ። ለአብነት ያህልም ወያኔ ስልጣኑን በዴሞክራሲያዊ መንገድ እንደማይለቅ የተገነዘቡ "የኢትዮጵያ አርበኞች ግንባር" በሰሜን ጎንደር፣ በወልቃይት፣ በጠገዴ፣ በአርማጭሆ፣ በሁመራ እንዲሁም በተለያዩ የሃገራችን ቦታዎች በሽምቅ በመግባት የወያኔን ውድቀት ለማጣደፍ በሰፊው ዘመቻ ተያይዞ ይገኛል።

የታሪክ አተላ የሆነውን የወያኔ መንግስት ለመታገል ምንም አማራጭ የሌለው የትጥቅ ትግል መሆኑን የተገነዘቡ ንፁህ የኢትዮጵያ ልጆች የዜግነት ግዴታቸውን እየተወጡ መሆኑን በቁርጠኝነት ሲያሳዩን እኛም ከኢትዮጵያ ህዝቦች አርበኞች ጎን በመቆም ዘረኛውን ወያኔን ከጭንቅላታችን አውርደን በመጣል የዜግነት ግዴታችንን በመግለፅ እኛም ከጎናቸው ልንቆምላቸው ይገባል።

ዛሬ የኢትዮጵያ ህዝብን በሃይማኖት፣በጎሳና በዘር መከፋፈል ብቻ ሳይሆን የብቅላ መረቡን በሰፊው በመዘርጋት በኢኮኖሚ፣በማህበራዊና በፖለቲካ በመከፋፈል የራሱን የምርጫ ጊዜ ከግብረአበሮቹ ጋር በመሆን ከፍተኛ ሚና ይጫወታል።

ለሃገር ነፃነት እየተባለ የስንቶቻችን አባቶች፣የስንቶቻችን ወንድሞች እንደወጡ በዛው ቀርተዋል።የስንቶቻችን እህቶች ለባዕድ ሃገር ስደት ተዳረጉ?የስንቶቻችን ሴት እህቶቻችን በወያኔ ወታደሮች በየጨለማውና በየእስር ቤቱ ደማቸው ፈሶ፣ተደፍረው ስነ ልቦናቸው ተነክቶ ተበላሽተው ይገኛሉ?ስንቶቹ አያቶቻችን ያለጧሪ ሜዳ ላይ ወድቀው ቀርተዋል። እንግዲህ ህሊና ያለው የአለም ህዝብና የኢትዮጵያ ህዝብ ለትዝብት ፍርድ ይስጠን።

እንግዲህ ወገኖች የኢትዮጵያውያን መብት ተነፍጎ የሃገር ሉአላዊነት ተናግቶ ነፃነት አጥቶ የሚመለከት ህሊና የሌለው ሰው ያለ አይመስለኝም።

ማንም ሰው ከነፃነትና ከባርነት ምረጥ ቢባል መልሱ ነፃነት ነው። ነፃነትን የፈለገች ህሊና ብዙ መስዋትን ትከፍላለች፤ህያውም ሆና ትኖራለች።በመጨረሻም አደራ የምላችሁ ኢትዮጵያ ሃገራችንን ወዳጅ በሙሉ አገራችንን ከንደዚህ አይነት ሰቆቃ ለመታደግ የአርበኞች ግንባር በንቁ እስከመጨረሻው የሚንቀሳቀስ አገር ወዳጅ ለወደፊት አላማና ህልም ያለው ፓርቲ ስለሆነ ሁላችንም ከጎኑ በመቆም አላማችንን እናሳካና አገራችንን ከባርነት እንታደጋት!

# ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ

**Dawit Tesfaye/Hadamar**

መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ፆታ፣ዕድሜ፣ሃይማኖት፣ጎሳና ዘር ሳይለይ ላለፉት ዘመናት በተለይም በአምባገነኖቹና በጨካኞቹ የመንግስቱ ኃ/ማርያምና የመለሰ ዜናዊ ስርዐቶች እንደባዕድ ወራሪ በገዛ አገሩ ላይና ልጆቹ ላይ የግፍ ግፍ ሲፈፀምበት ምድሪቱም በደም ጎርፍ ስትታጠብና ሁሉም የሚቻለውን በአቅሙ እነዚህ የሰው አውሬዎችን ከላዩ ላይ ለማስወገድ ሲኳትንና በመራራ ትግሉና በውድ ልጆቹ መስዋዕትነት የመጀመሪያውን ጭራቅ አስወግዶ ሁለተኛውን እኩይ ሲተካ ሃዘኑ ያልጠናበትና ፈጣሪውን ያላማረረ ኢትዮጵያዊ የለም። ይሁንና ሁልጊዜም ታሪክ እንደሚዘክረውና ድርሳናት እንደሚነግሩን "በጨለማ የነበረ ህዝብ ብርሃን አየ" ነውና በጭቆና ውስጥ ያለን እኛ ኢትዮጵያውያን ይዋል ይደር እንጂ ነፃነታችንን መቀናጀታችን ሳይታለም የተፈታ ነው።እነሆ ዛሬ የአምባገነኑ መለስ ዜናዊ ጨቋኝ ስርዐት የጀመረውን የግፍና የጥፋት መንገድ ሳያጋምስ "በሃያሉ የኢትዮጵያ አምላክ እጅ ለፍርድ ተይዟል።"ይሁን እንጂ ይህ እኩይ ስርዐት በህዝባችን መካከል የዘራቸው የጥላቻ፣ የበቀል፣ የክህደትና የመለያየት መርዞች ስራቸውን እየሰሩ ይገኛሉ። በተለይም የብሔርተኝነት፣ የጎሰኝነት፣ የጎጠኝነትና ብሎም የመንደርተኝነት መርዙ ምን ያህል የከፋ መሆኑን ባለፉት 21 የሰቀቀንና የጭንቅ አመታት ሬት ሬት እያሉን አጣጥመናቸዋል። ይበልጡንም ወንድማችንና ጋሻችን የሆነው ጨዋው "የትግራይ" ህዝብ በስሙ በመነገድ ከሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ ለመነጠልና ሌሎች ብሔረሰቦች በጠላትነት እንዲነሳሱበት ለማድረግ ያልተቆፈረ ጉድጓድና ያልተሸረበ ምድራዊ ሴራ አልነበረም። ነገር ግን የህዝባችን አንድነትና ፍቅር የተሸረበበት ድር የእልፍ አእላፋት ትውልዶች ለአንድነትና ለነፃነት በተሰዋ ንፁህ ኢትዮጵያዊ ደም በመሆኑ የከፋፋዮቹ ህልም እስከ አሁኗ ሰዓት ድረስ ሊሳካ አልቻለም። የተመኙትንም ኢትዮጵያን የማፍረስና ህዝቧን የማጫረስ ፋሽስታዊ ተልኮና ህልም ሳያሳኩ ወደ ጥልቁ "በአቦሸማኔ" ፍጥነት እየተምዘገዘጉ ይገኛሉ። በአሁኑ ሰዓት በሃገራችን የተፈጠረውን ታሪካዊ ክስተት የአምባገነኖቹ ቡድን እንዳይቀለብሰውና ወደ ህዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ስርዐት ሊደረግ የሚገባውን ታሪካዊ ጉዞ እንደለመዱት ለእኩይ አላማቸው መጠቀሚያነት እንዳያውሉት ህዝባችን ነቅቶ ሊጠብቅ ይገባል። ሁላችንም ልክ እንደአባቶቻችን ሃገራችንና ህዝባችንን ከሁሉ ነገር በላይ በማስቀደም በአንድነታችን በፍቅር ፀንተን በመቆምና በማስተዋል እኩይ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የዘራውን የመጠፋፋት መርዝ ፍፁም ሰላማዊ በሆነ መንገድ ከስር መሰረቱ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ማፅዳት ታሪክ የጣለብን አደራና ፈተና ነው ብሎ የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር ያምናል።

ስለዚህ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ጠላቶቹ ያቀበሉትን የመለያየት አጀንዳ በማጥፋት ለነፃነቱ መከበር በአንድነት በመቆም ለህዝባዊ ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ስርዓት በፅኑ እንዲታገልና በእጁ የገባውን ይህን ታሪካዊ አጋጣሚ ዳግም ለአንባገነናዊ ስርዓት አሳልፎ እንዳይሰጥ የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር ወገናዊ ጥሪውን ከታላቅ አክብሮት ጋር ያቀርባል።ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!

# አምባገነንነት ይብቃ

Betelhem Alemayehu / Würzburg/

በአሁኑ ሰአት በሃገራችን ያሉት ችግሮች ይሄ ነው ተብለው የተጠቀሱት ባያበቁም ከነዚህ መካከል በአሁኑ ሰአት በመኖሪያ ቦታቸው እየተፈናቀሉ ያሉ ኢትዮጵያዊያን ብዙ ናቸው በደቡብ ክልል በአማራ ብሄር በሆኑት እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ተወልደው ካደጉበት ንብረትና ልጆች ካፈሩበት ቀያቸው ባዶ እጃቸውን በወያኔ ካድሬዎች ተፈናቅለዋል። እንዲሁም በአሁኑ ሰአት ጋዜጠኞችን ካለምንም ጥፋት አስረው ካንገላቷቸው በኋላ የእድሜ ልክ እስራት ፈረደውባቸዋል፡፡ በእስር ቤትም እየማቀቁ ይገኛሉ፡፡ ይህ የወያኔ መንግስት ህብረተሰብን ማመሰቃቀል፣ እርስ በእርስ ማጋጨት፣ ታዳጊው ትውልድ ሃላፊነት እንዳይሰማው በማድረግና ቀማኛ እንዲሆን ሁኔታዎችን በማመቻቸት ትልቅ ተግባሩ ሆኗል፡፡

ኢትዮጵያ ለብዙ አመታት ያቆየቻቸውን ሃይማኖታዊ ቅርሶችና ትላልቅ ለም መሬቶችን መሸጥ ጀምሯል፡፡ በአሁኑ ሰአት በዋልድባ ትልቅ ገዳም በውጭ ሃገሮች ሸጦ እዛ የሚኖሩ ሞሎክሴዎች የትም እንደ አፈር በትኖአቸዋል፡፡ ይሄ ራስወዳድ መንግስት ነው እንጂ ለአንድ ትልቅ ሃገር ለ82 ሚሊዩን ለሚሆኑ ሕዝቦች አስተዳዳሪ /መንግስት/ በጭራሽ ሊሆን አይችልም፡፡ በልተው ካልጠገቡ የሃገሬ ዜጐች እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊያን ለአባይ ግድብ እያለ ከእለት ጉርሱ ከአፍ ላይ እየነጠቀ ለራሱና ለግብራብሮቹ ኪስ ማደለቢያ አድርጓል፡፡ ይሄ ጨካኝ መንግስት ዘረኛ ቡድን እነሆ ኢትዮጵያን በብሄር በቋንቋ እና በሃይማኖት ከፋፍሎ በመበታተን ኢትዮጵያን ለማጥፋት ስውር አጀንዳ ቀርጾ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ተብሎ መጠራት እንዳይኖር ለዘመናት በአንድነትና በፍቅር እንዲሁም በትውልድ የደም ሃገር ተሳስረው የኖሩ ህዝቦችን ከፋፍሎ መግዛት በጭካኔ የዘረኝነትን ውሃ ማጠጣት ከጀመረ ብዙ አመታትን አስቆጥሯል፡፡ ብዙ እጅግ በጣም ብዙ በቁጥር ይሄ ነው ተብሎ የማይጠቀሱ ኢትዮጵያዊያንን ከሃገራቸው አስወጥቶ ለስደትና ለሞት አብቅቷቸዋል፡፡ ውድ አንባቢዎች ይሄ ጨካጭ መንግስት በዚህ እንዲያበቃው በአንድ ላይ በመሆን ድምጻችንን ከፍ አድርገን በማሰማት የውድ ሃገራችንንና ህዝቦቻችንን ሰላም እና ፍትህ እናስፋ፡፡ድል ለሚጨቆነው ለኢትዮጵያ ህዝብ!

# በአምባገነኑ የወያኔ መንግስት ህዝቡ ሰላምና ነጻነት አጥቷል!

Nejat Sied Ebrahim /Treysa

ሃገራችን ኢትዮጵያ ሰላምና ዲሞክራሲ ሰፍኖባት ሕዝቦቿ በእኩልነት ሲኖሩ ማየት የሁሉም ውድ ኢትዮጵያዊያን ዜጐች ምኞት ነው ነገር ግን ላለፉት 20 አመታት ይሄ ምኞት ተግባራዊ ሊሆን ቀርቶ ጭራሽ ተቃራኒው እየተከናወነ ይገኛል። በዚህም ድርጊት በውስጡ የተከፋው ህዝብ በተለያዩ መድረኮች ተቃውሞን ሊያሰማ ቢሞክርም ሳይሳካለት በአንጻሩ ግን የአምባገነኑ ኢሕአዴግ መንግስትና ጭፍሮቹ ኪስ በሕዝብ ገንዘብና ቅሪት ሞልቶ ይገኛል፡፡

በዚህ ማስረጃ ለማግኘት ብዙ መኳተን አያስፈልግም በአዲስ ኢንቨስተር ንግድ ለመክፈት የሚፈልጓት ጊዜ ከኢሕአዴግ መንግስት የሚቀርብለት የ``Share`` ጥያቄ ስላላቸው ኢንቨስተር የኢቨስትመንት ቦታውን ወደ ተለያዩ ጐረቤት ሃገሮች እየቀየረ ይገኛል፡፡ ይህ ደግሞ ለኢትዮጵያ ትልቅ የኢኮኖሚ ውድቀት እያስከተለ ነው፡፡ ይባስ ብሎ እውነቱን የዘገቡትን ጋዜጠኞች በአሸባሪነት በመፈረጅ ወህኒ ቤት እየወረወረ ይገኛል፡፡ ይህ ሁሉ የሰለቸው ሕዝብ ሃገሩን ጥሎ ስደትን ከጀመረ አመታት ተቆጥረዋል፡፡

የወያኔ መንግስት ይሕ አልበቃ ብሎት እድሜውን በማርዘም ህዝብን በዘርና በሃይማኖት በመከፋፈል ሰላምን አሳጥቷል፡፡ አንባገነኑ የወያኔ መንግስት ሕገመንግስት ላይ በአስቀመጠው መሰረት ሃይማኖቶችን በራሳቸው ሕግና ደንብ መንግስት ጣልቃ መግባት እንደሌለበት ይናገራል፡፡ ነገር ግን እየተደረገ ያለው በጣም አስፈሪና አሳዛኝ ነው፡፡

በአሁኑ ግዜ በሙስሊሙ ህብረተሰብ በሙስሊም ስም ሆን ብሎ አክራሪ እያለ በሚጠራቸው ራሱ በአዘጋጃቸው አሸባሪዎች ሕዝብ በሰላም ሰላቱን ሰግዶ እንዳይገባ በአንዋር መስጊድ እየተደረገ ያለው ረብሻ ትልቅ ምስክር ነው፡፡

እንዲሁም ሙስሊሙ ህብረተሰብ የማይወክሉ እራሱ መርጦ ያስቀመጣቸው የአመራር አካላትን ሕዝብ እኛን አይወክሉም ብሎ በመቃወሙ እየታሰረና እየተንገላታ ይገኛል፡፡

እንዲሁም በክርስቲያን ሃይማኖት ለዘመናት ተከብሮ የቆየውን ጥንታዊ ገዳም በልማት ስም በማፈራረስና ታሪክን ቅርስን ለማጥፋት የሚያደርገው ዘመቻ ይሕንን የተቃወሙትን የሃይማኖት አባቶችን በማሰርና በማሳደድ ላይ ይገኛል፡፡

አምባገነኑና ዘረኛው መንግስት አገራችንን ወደ አስከፊ ችግር እየከተተ መሆኑን ለሁሉም ኢትዮጵያዊያን ግልጽና የማይካድ ሃቅ ነው፡፡ በሃገራችን ችግርና ረሃብ ጠፍቶ ሰላም የሰፈነበትና የተሻለች ኢትዮጵያን ማየት የምንችለው ሁሉም ዜጋ በዘርና በሃይማኖት ሳንለያይ እጅ ለእጅ ተያይዘን አንባገነኑን መንግስት ከስሩ ለመጣል ሁላችንም በአንድ ላይ በመነሳት ነው፡፡

# ትግላችንን በያለንበት ቦታ ሆነን እንቀጥል

Michael Asefa /Schweinfert

የኢትዮጵያ መሪዎች እኔ ብቻ ልግዛ ማንም ስልጣኔን ከእኔ መውሰድ አይገባውም በሚል አስተሳሰብ በትምክት የተወጠሩ የሕዝብ በድህነት መኖር በረሃብ በችግር በበሽታና በመሳሰሉት ምንም የማይሰማቸው ገዥዎች እነሱና ቤተሰባቸው እንዲሁም ደጋፊዎቻቸው ብቻ ተንደላቀው እየበሉና እየጠጡ ልጆቻቸውን የደሃው ገንዘብ እያስተማሩ መኖር የሚፈልጉ አይነት መሪዎች የተሟላች ሃገር መሆኗን በገሃድ የሚታይ እውነት ነው፡፡

ምንም እንኳን እነዚህ ድምጾች ከብሄራዊ መዝሙር በበለጠ በየቀኑ የሚሰሙ ቢሆንም ዋናው ባለጉዳዩ አምባገነን ኢሕአዴግ ግን ሊሰማቸው አይፈልግም አለመፈለግም ብቻ አይደለም እንዲህ አይነት ድምጾች የሚያሰሙትን በመወንጀል በመፍረድ በማስፈራራት በማሰርና በማሳደድ ስራ ላይ ተጠምዷል፡፡ በአጠቃላይ በሃገሪቷ ላይ ሮሮአቸውን የሚያቀርቡ በሙሉ "ጸረ መንግስት " ፣ ጸረ ልማት ተብለው እየተወገዙ ይታሰራሉ ይገረፋሉ፡፡

ለምሳሌ ባለፈው በ G8 አገሮች በተካሄደው የምግብ ዋስትና ስብሰባ ላይ የኢትዮጵያ አምባገነን መንግስት በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ረሃብ ችግር ሁኔታ የተመለከተ በሃገሪቷ ያለውን እውነታ ማር በመቀባት አለሳልሶና አሳስቶ ስር የሰደደ የተመጣጠነ ምግብ እጦት በማለት ሸፍኖ በኢትዮጵያ በተደጋጋሚ ለሚከሰተው ችግርና ምስኪኖች እልቂት መጥፎ አስተዳደር በ G8 ስብሰባ ላይ አለመወቀሱ ያሳዝናል ግን እኔን የሳበኝ በG8 ስብሰባ ላይ ጋዜጠኛ አበባ ገላው በጠቅላላ ሚኒስተር መለስ ዜናዊ ላይ የወረወራቸው ቃላት እንደሚከተለው ነው "መለስ ዜናዊ አንባ ገነን ነው የሰዎችንን ሰብአዊ መብት እየጣሰ ነው የምግብ ዋስትና ያለነጻነት ዋጋ ቢስ ነው፡፡,,, ነጻነት ነጻነት ኢትዮጵያውያን ቅድሚያ የምንፈልገው ነጻነት ነው " ቃላችን እውነትን የሚገልጹ ናቸው፡፡ ቃላቶቹ ግን እውነትን ስለሚገልጹ ጠቅላይ ሚኒስትሩ አንገቱን ደፍቶ ወደ ሃገሩ ተመልሷል፡፡

ከሰሞኑ ኢትዮጵያዊያን በሃገራቸው የተነፈጋቸው በነጻ ኢንፎርሜሽን ከተለያዩ ነጻ ሚዲያዎች ማግኘት እንዳይችሉ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሚቻለው ሁሉ በማገድ ላይ ይገኛል፡፡ የኢትዮጵያ መንግስት ማንኛውም የኢንፎርሜሽን ልውውጥ እንዳይኖር ኢትዮጵያውያን ከአለም ሁኔታ ተነጥለን እንድንኖር በማድረግ ላይ ነው፡፡ ምንም እንኳን በኢትዮጵያ ብዛት የሰው ቁጥር ያለባት ሃገር ብትሆንም እርባና ቢስ የሆነ መዋቅር ያላትና መንግስት የቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎት በሞኖፓል የያዘበት ሃገር መሆኗ ዲጅታል ሚዲያውን ከእድገትና የህብረተሰብን ተጠቃሚነት እንዲያቆለቁል ያደረገ ነው፡፡ በሃገሩም ካሉት ሃገር በሙሉ የኢንተርኔት ተጠቃሚዎች አነስተኛ ቁጥር ያለባት ሃገር ናት የኢንተርኔት መቆጣጠሪያ መሳሪያ ያስገባች ለዚያውም ለተሻለ የሃገር፣ የህዝብ አገልግሎት የሚችለው ገንዘብ የህዝብን መብት በማፈን ላይ ይገኛል፡፡ በ2005 ምርጫ ተቃዋሚዎችን ከስር መሰረቱ ምርጫውን ካሸነፈበት ጊዜ አንስቶ አጸያፊ ተግባር በማከናወን ላይ ነው፡፡ አንዱ ዜጋ እስካይፒ ኮምፒውተር ስልክ በመጠቀሙ ብቻ አስረ አምስት አመት ይፈረድበታል፡፡ ይህም የሆነው ሕዝብ ምንም ሃሣብ እንዳይኖረውና ንግዱን ሆን ብሎ በሞኖፓል ለመያዝ ሲል ያደረገው ደባ ነው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎችና እንዲሁም የነጻው ፕሬስ ጋዜጠኞችን በሽብርተኝነት ስም እየከሰሰ ለእስር ከመዳረጉም በላይ የፖለቲካ እስረኞች በእስር ቤት ውስጥ ከፍተኛ ድብደባ ይፈጸምባቸዋል፡፡ ለምሳሌ በጋዜጠኛ አንዷለም አራጌ የተፈጸመው ድብደባ ለዚህ በቂ ምስክር ሊሆን ይችላል፡፡

ስለሆነም ለመብታችን ለነጻነታችን የሞት ሽረት ትግል ውስጥ ለዘረኞች አንዳንዶቻችን ሊያስሩ ወይም ሊገሉ ይችላሉ ሆኖም ነገር ግን የማያውቁትን እውነትን የሚረግጧት ፍትህን ከሁሉም በላይ ደግሞ ነጻነትን የመኖር ጽኑ ፍላጐትን ሊገድቡ አይችሉምና የኢትዮጵያ ሕዝብ በዘርና በሃይማኖት ሳንከፋፈል እንደ አረብ አገሮች ትግላችንን በማቀጣጠል አንባገነኑን የወያኔ መንግስትን ተባብረን በአንድነት ማስወገድ ይገባናል፡፡ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር

# የነጻነት ጉዞ

**Asegedew Goshu, Netsanet/Oberursel (TS)**

በሀይማኖትና በተለያሀየ ጉዳዩች እየታመሠች ያለችው ሀገራችን ኢትዮጵያ፤ የወያኔ ነገር አሁንስ አበቃለት የሚያሠኝ እየሆነ ከመጣ ቆይቷል፡፡

አዎ ልክ ነው የሙስሊም ወገኖቻችን ድምጽ አልሠማ ብሎ እንዲያውም አፈና፣ ድብደባና ዛቻ እየደረሰባቸው ሲሠቃዩ ማንም አቤት የሚላቸው አላገኙም፡፡ እንዲያውም የሙስሊሙን ተወኳዩች በማፈንና አርፈው እንዲቀመጡ አስፈራርቷል ይህም ሆኖ ግን በዚሁ ሠሞን ነበር ፌዴራሎች አጃቢ በሆኑበት በአንዋር መስኪድ በ100 ሺ የሚቆጠሩ ሙስሊሞች በመሠብሰብ ተቃውሟቸውን ለመግለጽ ሞክረዋል፡፡

ሌላው ደግሞ እውነትም ፍትህ በኢትዮጵያ የለም የሚያስብለው የእነ አንዷለም አራጌ የፍርድ ሁኔታ ነው፡፡ እንደሠማነው ከሆነ ከስምንት አመት እስከ እድሜ ልክ የሚያደርስ ፍርድ ወያኔ አስተላልፏል ይህንንም የአለም አቀፍ የጋዜጠኞች መብት ተንከባካቢ ድርጅት / ሲፒጄ/ በአፍሪካ ዋና ተወካይ መሀመድ ኬታ እንዳሉት "ፍርዱ የኢትዮጵያ እድገትና መረጋጋት ህዝቡን በሃይል በማፈን የተገኘ መሆኑን" የሚያመለክት ነው ብለዋል፡፡ የአውሮፓ ህብረት በዚሁ የፍርድ ሁኔታ ላይ ወያኔ ሽብርተኞች ባላቸው እውነተኛና ታማኝ ጋዜጠኞች ላይ ያስተላለፈውን ውሣኔ አውግዟል፡፡

በሀገራችን ኢትዮጵያ እየታዩ ያሉ የተለያዩ ችግሮች እየተባባሱ እንጂ መፍትሄ ሲገኝላቸው አላየንም፡፡ ታዲያ የዋልድባ ጉዳይም ከዚሁ የሚፈረጅ ነው፡፡ በ19-07 -2012 በፍራንክፈርት ለሁለተኛ ጊዜ የተደረገው ዋልድባን ለመታደግ የተደረገ ሠልፍ ነበር፡፡ ከበርካታ ቦታዎች የተሠባሠቡ ምእመናኖችና አባቶች በመሠባሰብና አባቶች ባደረጉት የጸሎት ቡራኬ የተጀመረ ነበር፡፡ በመጀመሪያው ሠልፍ መልስ ስላልተገኘና አሁንም በዋልድባ ገዳም ላይ እየተደረገ ያለው የታሪክና የሃይማኖት ጥፋት መልስ የሚጠይቅ ሠልፍ ነበር ወያኔ የኔ የሚላት ኢትዮጵያ የለችውም ማለት ነው እንደዛማ ቢሆን ያለንን ታሪክ፣ እምነት ሃብት፣ ቅርስ ባጠቃላይ ህልውናችንን በጠበቀልን ነበር፡፡

አዲሲቷን ኢትዮጵያ እንዳለች በማቆየትና ሁላችንም አንድ በመሆን ታሪካችን እናስተካክል ምክንያቱም ሁላችንም ባለን ነገር በእውቀት በፀሎት እንዲሁም የአንድነት ጉልበታችንን በማጠናከር ኢትዮጵያ ሃገራችን ላይ እየደረሰ ያለውን አጸያፊ የአገዛዝ ተግባር በቃ ካላልን ነገ ዞሮ መግቢያችን የሆነችውን ሃገር ከዚህ በባሰ ሁኔታ ውስጥ ከመግባት እናድናት እላለሁ፡፡ ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር

# ማንም ከተጠያቂነት አይድንም

Beruk Yared Getnet /Haundorf

ወያኔ እራሣቸውን የጀግንነታቸው ምንጭ ደግሞ ዘረኝነታቸው እንደሆነ የስነልባና ችግር ያለባቸው ሰዎች ስብሰብ ነው፡፡ እነዚህ ድውያን በውስጣቸው ባለው የትንሽነት ስሜት ምክንያት በአስተሣሠብም ሆነ በሙያ የሚበልጣቸውን ሰው ማዋረድ እና ማሠቃየት ያስደስታቸዋል፡፡ እነዚ ሰዎች በሃብት እንጂ በመንፈስ አላደጉም እና እራስን ከሌላው ጋር እኩል አድርጐ የማየት ብቃት እና ሆደሠፊነት ማዳበር አልቻሉም፡፡

መንግስትን ለመገልበጥ ሙከራ አድርጋቹሃል በሚል በወያኔ ተከሠው እየተሰቃዩ የሚገኙ ወገኖቻችን ላይ አስከፊ ሰቆቃ እየደረሰ ያለው ይኸው ከመንፈሰ-ትንሽነት የሚመነጭ የስነ ልቦና ቀውስ ነው፡፡

ሰቆቃ መፈፀም አለም አቀፍ ወንጀል ነው በመሆኑም ዛሬ ወገኖቻችን ላይ ዘግናኝ ሰቆቃዎች በማድረስ ላይ የምትገኙ የወያኔ ቅጥረኞች በሙሉ ነገ በገባቹበት ገብተን ዋጋቹን እንድታገኙ የምናደርግ መሆኑን በጥብቅ ልናሣስባቹህ እንወዳለን ሰቆቃ ፈጽሞ ማምለጥ እንደማይቻል በቅርብ ካየችሁት ከሊቢያው መሪ ጋዳፊ ትምህርት ውሰዱ፡፡

ሰቆቃን እና የዘር ጥላቻን አድበስብባቹህ የምታልፍ የወያኔ ካድሬ፣ ዳኞች፣ አቃቢያነ ህግ፣ ፖሊሶችና ሌሎችም ሹማምንት ተገቢውን ቅጣት የምታገኙበት ቀን ቅርብ ነው አይርቅም፡፡

ወያኔን የማስወገድ ሃላፊነት የወደቀው በማንም አይደለም በኛው በራሣችን በኢትዮጵያ ልጆች ነው የበደሉ ገፈት ቀማሽ በሆንነው በኢትዮጵያ ህዝብ ትግል ነው በታሣሪዩች እና በሌላውም ህዝባችን ላይ እየተፈጸመ ያለው ሰቆቃ እንዲያበቃ ወያኔን ከስልጣን ማባረር እና በምትኩም ለሰባዊ መብቶች ክብር ያለው ፍትሃዊ ስርአት መመስረት ይኖርበታል፡፡

ዘር ላይ ያነጣጠረ ጥቃትን ማድረስ በሰባዊነት ላይ የሚፈጸሙ አለም አቀፍ ወንጀሎች በመሆናቸው ይዋል ይደር እንጂ የማይቀርና በይቅርታ የማይታለፍ ተጠያቂነትን በውስጣቸው ይዘዋል፡፡ በነዚህ ወንጀሎች የተሣተፋችሁ ሁሉ መጠየቃቹህ በፍጹም አይቀርም ያቀን ደግሞ ቅርብ ነው፡፡ ያኔ ታዝገቴ ነው የፈጸምኩት ማለት አይሠራም፡፡ ሽራፊ እንኳን ህሊና ያላችሁ ካላቹህ እጃችሁን ሰቆቃ ከመፈጸም አውጡ ሰቆቃን አጋልጡ፣ ለሃገራቹህ ነጻነት ታገሉ አለበለዚያ ግን የህዝብ ቁጣ በናንተ ላይ ይወርዳል፡፡

በመጨረሻም ለሠፊው የኢትዮጵያ ህዝብ እማስተላልፈው መልዕክት ቢኖር አሁን ያለው አምባገነኑ የወያኔ መንግስት ከስልጣን እስካልወረደ ድረስ በገዛ አገራችን እንደዜጋ የመኖር መብት የለንም ስለዚህ ይህንን መንግስት ከስልጣን ለማውረድ ሁላችንም እንነሣ ከአሁን በኋላ ወደፊት እንጂ ወደኋላ አንመለስም ሃላፊነት ይሠማን ወያኔን ለማስወገድ ቆርጠን እንነሣ፡፡ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!

# ጎጂ ልምዶችን ያባባሰ ስርዓት-ወያኔ/ኢህአዴግ

Hanna Nigusse/Meseret Kebede- ARNS-BERG

በኢትዮጵያ በከፍተኛ ደረጃ ከተባባሱት ጎጂ ልምዶች መካከል የሴት ልጅ ግርዛት ዋነኛው ነው።በዚህ ችግር በገጠር ብቻ ሳይሆን በከተማም ያሉ ሴት እህቶቻችን ራሴንም ጨምሮ የችግሩ ሰለባ ሆነናል።በዚህ ችግርም ከፍተኛ የሆነና የማይሽር አዕምሮአዊ ጠባሳ ጥሎብናል። ይሄንን ስር የሰደደ ችግር ደግሞ ለማጥፋት ይቅርና ለመከላከል እንኳን ከውጭ አገር በተገኘ እርዳታ እንጂ የወያኔ መንግስት ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥቶ በጀት እንኳን ይዞለት አያውቅም።

ይህ ደግሞ የመንግስቱን ግድየለሽነትና ለሴቶች ጉዳይ ቢሮ ማቋቋም እንጂ መሰረታዊ ጥቅማቸውን ሲያስጠብቅ አይስተዋልም፡፡ስለዚህ የሴት እህቶቻችንን ችግር ለማስቀረት ያልቻለው ወያኔ በተዘዋዋሪ በሴቶች ላይ ሞት በይኗልና በዓለምአቀፍ ህግ ሊጠየቅ ይገባል።የወያኔ ተግባር በዓለም አቀፍ ዘንድ ለፈረመው የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ ያለመገዛቱንም ያመለክተናል።ዜጎች ጤናማ በሆነ ሁኔታ እንዲኖሩ ከመንግስት የሚጠበቀውን አልተወጣምና የወያኔ/ኢህአዴግ አመራሮች ለህግ ሊቀርቡ ይገባል።

ወያኔ የፖለቲካ ችግር ብቻ ሳይሆን ማህበራዊ ቀውስም እንዲስፋፋ በተዘዋዋሪ ያገዘ ስርዓት በመሆኑ በወያኔ መቃብር ላይ ለሁሉም ዜጎች እኩል የሚያስብና ለደህንነታቸው የሚታገል ስርአት ለመገንባት በመላው ዓለም የምንገኝ ኢትዮጵያውያን በዋናነት ሴት ኢትዮጵያውያን በተለይ ችግሩን ላላወቁ ለማሳወቅና ትግሉን ለማፋፋም በጋራ እንነሳ እላለሁ።

# ነጻነት ያለው እኩልነት ይኑር

Yordanos Hilegeyorges /Lahntal

ዛሬ ለኢትዮጵያ ህዝብ ነጻነት እኩልነት የሃይማኖትና የጐሣ ልዩነት ሳይኖር ተቻችሎ ለመኖር የእኛ ኢትዮጵዊያን የሁልግዜ ምኞት ነው፡፡

ኢትዮጵያ ሃገራችን በሠላምና በፍቅር የመኖር ፍላጐቷ ሣይሟላ ሃይማኖት በሃይማኖት ላይ በማነሣሣት ወያኔ ትልቁን ሚና እየተጫወተ ይገኛል፡፡

በህዝባችን ላይ ነጻ ዲሞክራሲ ሳይኖር ተረግጠው ተገፍተው ይገኛሉ በእንዲህ እንዳለ የኢትዮጵያ ሕዝብ ወያኔ በግፍ በሃይል በጭቆና እያስተዳደረ ይገኛል፡፡

ወያኔ ለራሱ ፓርቲዎች ነጻነትን ሠጥቷቸው ነገር ግን ሌላውን ህዝብ ግን በእስርና በማንገላታት ላይ ይገኛሉ፡፡

የኢትዮጵያ ህዝብ በአገሩ ላይ ሆኖ እንደ 3ተኛ ወገን የሚታይበት ወንጀል የሚሠራበት ህዝብ ሆኗል፡፡ አባቶቻችን ተቻችለውና ተከባብረው የኖሩባትን ሃገር ወያኔ ግን ሙስሊሙን ከክርስቲያን እያለያየ ይገኛል፡፡

ለእኛ ነጻነት ብለው የታገሉ አሁን በእስር ቤት በጨለማ ክፍል በእስራት እና በወያኔ የደህንነት አባላት እጅ እየተሰቃዩ ያሉትን ውድ የኢትዮጵያ ልጆችን እናስብ፡፡ ለእኛ እንደታገሉልን ሁሉ ለእነሱ ነጻነት ስንል የሚያስፈልገውን መስዋእትነት እንክፈል ሁላችንም በአንድነት ድምጽ በቃ እንበል

So we have to unite and struggle until we wreck apart the burden of repression.

# Adios Freedom of Expression!

**Meskerem Eshetu/Hof**

On July 12, 2012 a one-party seat Ethiopian Parliament has ratified a new "Telecom Proclamation" on a ban of Voice over Internet Protocol (VoIP), like Skype, under cover story of national security. And anyone who violates this law will get a 15 year sentence in prison.

Albeit the fact that this law like "dictatorial order" was wrapped under the name of national security, its main purpose is to suppress the freedom of getting information and freedom of expression. After all, the Zenawi regime is one of the cold blooded governments that use a DPI (Deep Packet Inspection) technology to block websites and voice messages over internet. And this is completely against the value of democracy in which people have a right to get information and express themselves.

Following the persecution of Journalists along with this new "law", our people have been suppressed under absolute tyranny of Zenawi.

# Now at the end of dictator MELES ZENAWI!!!

**Yonas Tesfay/FULDA**

End of Meles should be end of power and resources abuse by the ruling Party in Ethiopia, the Woyane crimes and genocides, and human rights abuses in Ethiopia (specially Ogaden, Gambella, Amhara, Oromia and Afar regions), and return of unity and equity for such ethnic groups (like Oromos), so they can take their right position in the national reconciliation and development.

No accuses and compromises and also trade on the good governance, peace building and human rights issues of the Ethiopians. Ethiopians should learn from the past and their history, stop such groups under the banner of Christian or Islam in the government offices and institutions. Also, free elections and representation of the ethnic groups in the federal government institutions, freedom of the people and protection of the human rights principles, religious tolerance and peaceful-coexistence of the people, good governance, peaceful governance and resource utilization, unity and equity among the ethnic group; Ethiopian professionals and leaders are responsible to protect their people from being engaged in such devastating instigation and manipulation of reactionary elements.The Ethiopian government officials (including the EPRDF/TPLF groups and members at both federal and regional level, army, federal and regional police and liyu police officials) should face justice for the crimes they committed over several years and misuse of aid relief and donor funds in the Ogaden, Gambella, Oromia and Afar regions.

The next step should building peace and also good relationship and economic partnership with the people of the Horn of Africa region; especially with Somalia, Djibouti, Eritrea and Sudan.

# The time to be United!

**Mukedis Nuru/Ibbenbüren**

This is time to start united and coordinated struggle to save our homeland from the dictator TPLF/EPRDF regime

The so called Ethiopian prime minister Meles (Bucher) is in life and death so we have to fight the next dictator prime minister era from the TPLF

Freedom of religion is a human right which every citizen has the right to enjoy. Currently Ethiopian Muslims are struggling not only for their own religious rights but also for all of us, Ethiopians. They deserve bold support and sincere appreciation from their Christian and non-believer compatriots.

Coordinated Ethiopian opposition political forces has been the persistent demand of the Ethiopian people ever since the ethno-dictatorial regime of the Tigrian People's Liberation Front (TPLF) has ascended to power some 21 years ago. Thus far, this important but very demanding effort of united struggle of the opposition forces has been frustrated by several factors. However, given the stages of the contradictions in the country and the difficult circumstances our people are suffering.

Ethiopian opposition parties have responsibility to participate in united and coordinated manner for the current religious freedom movement in Ethiopia to over through the dictator TPLF regime; we have lost many opportunities to enjoy freedom because of scattered and fragmented struggles.

We Ethiopian Christian or Muslim we have to fight the TPLF/EPRDF dictatorship with united and coordinated manner to enjoy our goal- Freedom Freedom Freedom!

# Why Ethiopian cannot Revolt now?

**Rut Tesema/Fulda**

Ethiopian have neither aggressive activist nor faith full leader inside and outside the country. And in 3000 Ethiopia history, Ethiopian had never revolted and having lack of trust among different ethnic and tied back with lack of well organized for common purpose in their culture. so at this time it is too late to adapt that culture by the people with minimum way of communication ( the lowest internet access in Africa) so as quick to catch up the current tsunami of revolution across the Continent.

Moreover; the tyrant in Ethiopia have controlled all the website even blocked those website the regime think that they are threat of their existence. so i could comfortably say Meles and his genocidal gang will stay in power for the next two years minimum. till then the only option is just have to engaging him with AK47 so as to weaken his power till the people adapt the trust and rise to get ride of this blood suckers regime.

# No Democracy in Ethiopia

**Fekerte Wolde /Tirschenreuth**

Ethiopia is on the trajectory as parlament election approach 2005 and 2010 These would be the first national election since 2005 when post election protest re-

sulted in the dead of more protesters many of them victims of excessive use of force by the police.

Most people paid the unlimited price in 2005 for their peaceful protest against a rigged election and for justice and democracy in Ethiopia. About 300 individuals lost their lives during those peaceful demonstrations in Addis Ababa.

These might shed arose colored picture of my poor country while the Ethiopia Democracy or democratic Ethiopia is built on false premises and its house built on sand and its eroded from with in.

The peaceful leader on the surface has done nothing but threaten scolding and demeaning the people it claims to serve.

# Ethiopia is calling –The Time is now

**Elsa Hagos (Germany)**

Many dictators in Africa and also the current dictator of Ethiopia came to power through the barrel of a gun since he has no tolerance for dissent and his appitite for democracy is almost dead. In his 21 years in power zenawi has held three Shem elections and in May 2010 he concluded his fourth election, which is dubbed as one of the most lopsided election in one of the most diverse country of Ethiopia.

So at this time in Ethiopia still we couldn`t find a solution for what the woyane leaders have done against the Ethiopia people even to day. The blood of Ethiopia still flow on the ground. Many people are prisoned. it is not yet finished flowing the blood of innocent citizens those who are fighting against the rulling party. we could see that the rulling party, for its interest and also these woyane leaders have been stealing different resources. Ethiopian people must fight this Authoritarian party to have their inalienable human and democratic rights. We need democracy &freedom.

# The budget deficit of Ethiopia

**Yonas Asrat Woldesenbet / Frankfurt**

The approved government budget of Ethiopia for 2012/2013 Fiscal year was budgeted with out considering the present global economic crisis. The budget of Ethiopia is financed by external assitance and loan.

The budget deficit is higher than previous years the result of large capital budget tax evasion and the arbitrary powers of officials. For full filling the budget deficit the government of Ethiopia began minting which is not an appropriate action that is to be done is eliminating tax evasion and arbitrary powers of officials and reducing large capital budget creating growth. When the economy growing easy to handle budget deficit.

# Ethiopians Must Awaken, "BEKA!"

**Eyob Negwo/Windsbach**

The Arab Revolution or The Arab Spring was sparked by the first protest in Tunisia following the buring of a young Tunisian named Mohamed Bouazizi in protest of police corruption and ill treatment in 18 December 2010. This revolution escorted the overthrown of four dictators, Tunisian President Ben Ali, Egypt President Hosni Mubarak, The Libyan Leader Muammer Gaddafi and Yemeni

President Ali Abdullah Saleh. Currently the revolution is taking place in Syria and Sudan. People in those countries are saying enough for the dictatorial leadership because of corruption, lack of democracy and economic problems. The situations which make peoples rose in these countries are worse in our country than theirs.

The TPLF lead by dictator Zenawi is taking all the possible action to prevent this kind of revolution from happening in the country. Following the Arab Spring the dictator strengthened the security measures and jams the Ethiopian Satellite TV, ESAT, many Arab Sat broadcasts and international radio broadcasts like VOA (Voice of America) and Deutsche Welle (DW) radio for fear of the revolution.

The dictator Meles Zenawi said in parliament: "We are not worried that there will be a north-African type revolution in Ethiopia, it's simply not possible", on 12 march this year, with his customary "assurance" he continued by saying "The circumstances for it do not exist". In doing so he tried to give warning and divert the attention of the people. However, after this speech the TPLF junta arrested hundreds of individuals suspected of organizing a revolution. This indicates the fear and contradiction that has come prevalent amongst our dictators.

Enough!, "Beka!" amidst the Arab uprisings, is the watchword of popular uprising to the ruling gegime, which is unfortunately circulating around the country and internet. Awakening tracts has been circulating inside the country for a while now. In an earlier calling on the people to take on the streets on 28 May, 2011 failed due to heavy overnment crackdown. Even though the TPLF security forces were successful in the 2011 crackdown, the revolution which is around the corner seems irreversible.

The TPLF is aware of how information technology plays a role to trigger a successful reolution. Due to this the TPLF security strategy is being focused on eliminating any political blogs, website, radio and TV broadcast by spending millions of dollar to jam and block them. Last week the government ratified a new complicated telecom law which prohibited people not to use VOIP software like Skype, Google talk, Yahoo messenger and others in orde to control the flow of information.

In 2009, dictator Zenawi ratified Anti-Terrorism law to crack down any one who participates in the struggle for democracy. Recently around 24 journalist and political party leaders are convicted as terrorist with this so called law. As dictators further their die-hard efforts to try to protect their power, this is the perfect time to stand together and say "BEKA!" for the TPLF dictatorship.

# The New Anti Terrorism Law- A Weapon against Basic Democratic Rights in Ethiopia

Samuel Solomon /Bayreuth

Starting from their early years in power, the Woyane regime is using systematic suppression and censorship of free media which are a few news papers and magazines. Many journalists outlived and survived this obstacle by being cunning and courageous. Many more either fled to another country or shifted to another career. The likes of Andualem Arrage, Eskinder Nega, Firehiwot Alemu and many more continued to write and express their opinion in a democratic way.

But starting from 2011, in part by the fear of the spreading of the Arab Spring to Ethiopia and in the intention of containing it, the dictator leaders of Woyane began to suppress and imprison countless journalists as well as famous bloggers. Their excuse is the so called anti terrorist law which prohibits and restricts the expression of free opinion and critics towards the ill governance of the regime.

The ideology of the Woy-

ane regime and its cruel and out date governance has been already rotten. At this moment virtually all of the people of Ethiopia are aware of this fact. So, by being frantic cos of this fact, they developed a new strategic weapon which is suppressing and imprisoning free journalists whom the public adored.

We Ethiopians will voice our support for those journalists who are jailed and experiencing immense hardship. The only thing they have done is expressing their thoughts through public media in a democratic way.

The road to democracy is not far. Dictator leaders and their system of governance through terror and suppression is being scrambled as we saw in North Africa and the Middle East.

Freedom of Speech and Democracy in Ethiopia!!!

# The Events of Woyane State in Ethiopia

**Dina Ayalew/Windsbach**

Woyane that he was domed our democracy and brings the burdents in-humans. Woyane autocracy when he came to powe in 1983 up to still present time he is in the power, the way of the administration always in the undemocratic and attack negative thinking in the society. The Ethiopian societies have their different method the way to improve their living condition in order to living live. But the doing of woyane hid going would be the educated people they not accepting his administration because of he not looking the people in democratic way that the educated or civil servants they opposes the idea of woyane. So that peoples to bring freedom they fighting then the woyane theis opposes I must destroy this my opposers and showing afraiding giving the talented just stopping what the man or woman they are working in their working fields. Not only outing or throwing from the work fields, but also arresting which accused a person who is not doing wrongs.

Finally, i would like to urge the Ethiopian people to be united and avoid the dictator Woyane regime!!!

# Stop State Terrorism in Ethiopia!!!

**Bisrat Woldemicael/Bisrat Girir/ StadtAßlar**

Ruling a country by terror is wholly unacceptable both from democratic and human rights perspective. However after the EPRDF regime adopted an ambiguous "Anti-terrorism law", Journalists and opposition party leaders have been persecuted with no substantive evidence and reason. Besides the regime has employed the tactic: "terrorize one, and the rest will be kept in line" so as to subdue the rest of the people. So, we have to stop state terrorism in Ethiopia with our frantic effort!!!

# What comes next in Ethiopia?

**Debebe Kebede /Goch**

Ethiopia has clearly fallen on hard times. It is one of the poorest nations on Earth. It has suffered over the last decades from recurrent famine and political chaos brought on by drought, poor land management and strife between regions and ethnic groups. Opportunities for poor, rural Ethiopians-the majority of the population –to escape the grinding poverty of their lives remain rare and elusive. In the last 40 years, due to the very dictatorial nature of the Derge and Weyane regimes many of the best and the brightest immigrate to the United States and elsewhere, leaving Ethiopia with fewer and fewer people in a position to help steer the country in a positive direction. According to a recent study presented at the National Symposium on Ethiopian Diasporas, Ethiopia

has lost 75 percent of its skilled professionals during the past ten years alone. And even among those who stay, there is little agreement about what direction that should be followed.

Even though, there are a number of dynamic factors that makes the internal political situation of the country more volatile and vibrant, its strategic location between the Middle East and the rest of Africa and its cultural and historic links to both, make its fate a matter of global interest and concern. Yet most people who are familiar with the region find it difficult to predict its future and even more difficult to determine how best assist the country in solving its own problems.

Currently different sources indicated that Meles Zenawi is in a critical health condition According to these sources dictator Meles Zenawi is suffering from blood cancer and diabetes. But still, no official information is provided to the public about the health condition of the minister by the government. This makes tension to grow up in the country some people also started to believe that Meles Zenawi may be died. On the other hand, the conflict between the government and the Muslim community is cracked down from intimidation and detention to mass killings and torture.

This is most critical time to save Ethiopia from the politics of antagonism and famine. The writer strongly believes that national reconciliation among political parties and even between individuals will be the best solution to break the vicious circle of poverty and political turmoil. It is a matter of dialog and national conscious to achieve some middle ground-to preserve what is good about the past to build a strong nation in the Horn of Africa. We need to know that this is right time for the inevitable revolution!

# Unity and independence

**Abay Gedamu Tekle /Limburg**

To be successful in a struggle Against our enemy we oromo people need to empower our oromo liberation bleck that means we have to strew to give confidence and power to our selyes so that oromo people can do its self the job of liberation Tokummaa for Billsumman and by avoiding. All possible thigs which contribute to our division and to our weakening like the inner fighting we do have Against each other now will be the time of empowering oromo nation for the new start and for doing efficient struggle This will encourage us to strengthen O.L.F the only remaining options we have 1 think the only language weyane understand is the military or Amend struggle one call upan all oromus in oromia or Abroad to come together and remove meles from power once and for all we Ask international community to put pressure on this regine to step torturing innocent oromo Artists and students in particular and all oromo population in general this reging makes oromo arrests and tortures As every day business so we ask international community to speak up against these crime to exert pressure on the T.P.L.F regime. oromiya shall be free!!

# Diktatorische Regierung des Meles Regimes

**Kidest Zelalem /Köln**

**Zerstörung von kirchen und eines klosters geplant**

Das regime von premierminister Meles Zenawi und die ``Tigrayan people´s Front´´ bereiten die Enteignung und Zerstörung von 18 kirchen vor. Das über 1000 Jahre alte kloster Waldba bei Gondar soll mit Bulldozern der Erde gleich gemacht werden, in dem uralte,

sehr seltene schriften der orthodoxen Tewahedo-Kirche aufbewahrt werden (Yilma Haile Michael-Hinz, Journalist).

### Haftstrafe für Blogger in Äthiopien

Für 18 Jahre soll der Journalist Eskinder Nega ins Gefängnis. Gleichzeitig mit ihm wurden mehrere Regierungskritiker verurteilt, von denen viele allerdings im Exil leben. Das Gericht in der äthiopischen Hauptstadt Addis Ababa behauptet, der Blogger sei an einer verschoörung zum sturz der Regierung beteiligt gewesen und hätte in einer Terrororganisation mitgearbeitet.

Eskinder Nega war der Herausgeber mehrerer regierungskritischer Zeitungen in Äthiopien und erhielt vom amerikanischen PEN-Verband einen Preis für Meinungsfreiheit. Auch das sogenannte Anti-Gesetz, das zu zu seiner Verurteihung führte, hatte Nega zuvor kritisiert.

Äthiopian wird seit 21 Jahren von Premierminister Meles Zenawi regiert. Menschenrechtler werfen ihm wahlfälschungen und die Unterdrückung der Opposition vor.

Nicolas Henin, Arte-Korrespondent:

``Eskinder Nega hat auch Artikel über den Arabischen Frühling geschrieben und die mögliche Verbreitung in Afrika und Äthiopian. Journalisten können hier im Land nicht frei arbeiten. Die wenigen unabhangigen Zeitungen haben eine geringe Auflage. Radio ist weitgehend, Fernsehen vollständig staatlich. Die Anzahl der Internetnutzer ist eine der niedrigsten weltweit, das Internet wird stark kontrolliert.´´

So eine Regierung braucht überhaupt keiner, deshalb demonstrieren wir (Äthiopier), jeder zeit gegen diese diktatorische Regierung.Ich hoffe, bald wird das Meles Regime zu ende!!!Diktatorische Regierung des Meles Regimes

# The Key Elements of Good Governance

**Henok fantahun /Limburg**

For one country growth and sustainable development good governance is the basic and crucial way the term growth word is expressed in two side that is socio economic growth and political growth.

Governance means the management of the relations between government and its people within a given constitutional order.

Good governance is the responsible use of political authority to guide and coordinate a nation´s offer. In the other words it also expressed as it is a concept that use in political science public administration and development management it appears along side such terms such as democracy, civil society, participation, human rights and sustainable development.

Good governance is the opposite of bad governance, but if we consider the spread of corruption in governance unskilled man power, wide spread poverty and misery especially in the under developing and developing countries which are majorly caused by bad governance corruption is the major seourage preventing economic growth and stability for one country.

The four basic principal elements of good governance

**Participation** means the involvement of citizens in the development and

governing process i.e citizens could participate either directly or with their representatives to effect decisions regarding their country´s affairs.

**Transparency:** refers to the decisions taken and their enforcement are done in according to the rules and regulations it also expressed as enough information is provided and that it is provided in easily manner (understand able forms and media)

**Accountability;** is governmental institutions, private sector and civil society organizations are accountable to the public and the their institutional stake – holders.

**Rule of Law;** government enforces equally transparent laws. Regulations impartial enforcement of low requires an independent judiciary. In Democratic government there is good governance, good governance without participation, Transparency, Accountability, and Rure of law is bad governance.

# Woyane is still cheating the world!

**Tenalem Belayneh Zerihun/ Alsfeld**

Who knows the whereabouts of Dictator Meles Zenawi? Meles' sickness is just exuastion and he is taking extended vacation, then why Bereket and etal are dischargeing contradictory informations to their loyal media outlets? Why is he spending that much time in foriegn land while he could take the so called deservedvacationin Ethiopiaitself?

The truth of the matter is Meles is very ill and had a critical surgery and Bereket and et al are praying that his situation improves sooner than later. There is no doubt that Meles is indeed alive but his return to his job is very unlikely.

The main agenda behind of disseminating those confusing and contradictory information is due to the intense confusion that Bereket and et al find themselves -i.e, will meles get better soon? Will he be able to get back to his job? What if he didn't? How could break the news of succession to Ethiopian people? Mind you most of his generals are in dark as the people….because once they find out that Meles is incapable of resuming his duty, they will all fight for the power. Woyane/EPRDF is believed to be behind all these drama…sudden replacement could result unprecedented chaos then let us get the people used to seeing the country without Meles and then waiting the optimum time and we all knows that that optimum time is very sooner!!May God bless Ethiopia!!!

ግ
ጥ
ም

# የግጥም ቋት

ግ
ጥ
ም

## እስከ መቼ ልመና

Berekti Haile/Friedberg

እስከ መቼ ልመና ደጅ መጥናት ወያኔን
በረሃብ እየቀጣው ታታሪ ወገኔን
በአንድነት ተባብሮ ታግሎ ማስወገድ
ነው
ለአረመኔው ቡድን መፍትሄው ትግል
ነው
ከአመጽ ትግል በቀር ልመና እማይገባው
አገር አልባ ሆኗል ሕዝብ እየተሰደደ
የወያኔ ሴራ ስር እየሰደደ
ውሸቱን አልተወም ያኔ እንደለመደ
እስከ መች ልመና ሁሌ እሽሩሩ
ሕዝብ ነጻ እንዳይሆን ወያኔን እየፈሩ
ተማሪው ከትምህርት ነጋዴውም ከንግድ
መነኩሴው ከገዳም ሼኩም ከመስጊድ
ሁሉም ከቤት ይዋል አንዱም ስራ
አይሂድ
ወያኔ በስራው በአለም እስኪዋረድ
ማንም ሣይለያይ ዘር ሳይቆጣጠር
ወንድና ሴት ብለን ትንሽ ትልቅ ሳይቀር
የኛ ጩቋኝ ጠላት ከወያኔ በቀር
እስከ መች ልመና ወያኔን መታገስ
ቁጭ ብሎ ማየቱ ሃገርን ሲያፈርስ
በሆድ አዳሪዎች ዙሪያውን ተከቦ
ሕዝብን ሊበታትን ውስጥ ለውስጥ ሾርቦ
አገር አደኸየ አንጡራ ሃብቷን አልቦ

## ደረሰ ሰዓቱ !

Genet Zewdie/Duisburg


ደረሰ ሰዓቱ ግፍ የሚያበቃበት
በእውነተኛ ዳኞች የሚፈረድበት
በግፍ የታሰሩ የሚለቀቁበት
በቃ ሊያበቃ ነው የወያኔ ስራ
ግፍ የተሞላበት ያ ሁሉ መከራ
ወያኔ ደንግጧል ቀኑ ሲቀርብበት
ጉዱ ሊፈላ ነው ቀን ሲጨልምበት
ለኛ ግን ሊነጋ ሰማዩ ቀላልቷል
ፀሃይም ልትወጣ ጮራዋ ፈንጥቋል
ልናይ ነው ይህን ጊዜ ቀናቱ ተቃርቧል
አንድ ሁለት እያለ ማስቆጠር ጀምሯል
መዳህ የጀመረው የብርሃን ጮራ
ቆሞ መሄዱ አይቀር ልባችን አይፍራ
በቃችሁ ሊለን ነው ደጉ የእኛ ጌታ
ከደረሰብን ግፍ ሊሆነን መከታ
እርሱን ተደግፈን ሁላችን እንበርታ።

## መሪ ያጣች አገር

Michael Asefa Abebe /Bayreuth

መሪ ያጣች አገር ሕዳ የሌለበት
ጉዳይ ዘራፊው ሁሉ የሞላበት
ጠያቂ የሌለው የሰው ንብረት ሲዘርፍ
የሰው ሕይወት አጥፍቶ የነበረ በግፍ
ሁሌም የሚሞክር ምን ጊዜም የማያርፍ
ከቀበሌ አንስቶ እስከ ላይ አመራር
ጉቦ በመቀበል የሰከረ በብር
ፍርድ ይገባዋል ሊቀጣ ሊታሰር
መሪ ያጣች አገር ሕዝብ የተራበባት
በስሟ ለምኖ መሣሪያ ገዛበት
በስሟ ለምኖ ንብረት አፈራበት
ሊቀጣ ይገባዋል ፍርድ ሊበየንበት
ሕዝቡን ለስደት ደርሳ የሚኖር በቅንጦት
በደልን ፈጽሞ ሁሌ የሚኩራራበት
ባጠፋው ጥፋቱ ታሪክ ይፈርድበት
መኖር የለመደ ሕዝብን እያጋጨ
የውሸት እንባውን በከንቱ እየረጨ
አገር አደገ ይላል ሕዝብ እያናጨ
መሪ ያጣች አገር ፍርድ የጐደለባት
ሙሁሩ ተሰዶ ከአገር የወጣበት
በበደለው በደል ታሪክ ይፍረድበት፡፡

# ለንደን በአትሌቶቻችን ደምቃለች መልካም እድል እንመኛለን



# Bayreuth-Demonstration

On 17th of July 2012 a demonstration was held in Bayreuth City by exiled Ethiopians who gathered from Forscheim, Hof, Bayreuth, and Kronach. Following on the conviction and verdict of activists, Journalists and Opposition party leaders on July 13th of 2012 by the dictator Zenawi regime and the adoption of the new "Telecom Law", the congregates were clamouring in opposition by holding different slogans and by waving the Ethiopian Flag.












It was started from Wilhelm-Busch Street through Ludwig-Thomas Street and then to the front yard of Municipality ("Rathaus"). And there it was concluded by submitting a Petition and Explanatory Open Letter to the Mayor Office.By: Dawit Fanta




# ጥላ መፅሄት አራተኛ እትም

ጥላ መፅሄት አራተኛ እትሟን ይዛ October 30/2012 ለንባብ ትበቃለች። ስለዚህ አዳዲስና ነባር ደንበኞቻችን በአዲሱ አድራሻችን ታገኙናላችሁ። በመፅሄታችን ላይ ያላችሁን አስተያየትና መልዕክቶች ሁሉ እስከ October 20/2012 ድረስ ልታደርሱን ትችላላችሁ። ለበለጠ መረጃ የስልክ መስመራችንን መጠቀም ይቻላል።

## WIR SIND IMMER FÜR SIE DA!





አድራሻችን

Mesfin Abraha

Löhrgasse 4

36251 Bad Hersfeld

E-Mail: tilamagazine@yahoo.de

Web-Site: tilamagazine.yolasite.com

Tel.No. 0152- 22195567

0176- 59384456

0176- 68830082


## TILA MAGAZIN IST EURE MAGAZIN!